መስከረም 1 2014
ወርሀዊ
ESQUARE ADVERTISING

ቅንድል DIGITAL MAGAZINE

ቅንድል ዲጂታል መፅሔት

" . . . . አብረን ስንጓዝ ተገጫጭተን፣ ተገፋፍተን ሊሆን ይችላል።ለነገ ተስፋችን ስንል ግን ስብራታችንን የፍቅር ንቅሳት አድርገነው ወደፊት ልንጓዝ ይገባል . . . "

ድምፃዊ ሀይለየሱስ ፈይሳ

#ሀገሬ

ሀገር እንቁ ጣጣሽ - የሰር ክንድሽ አቅፎን !

በሀይሉ ወ/ይፍራው (መባ)

#አጃኢብ

ምኞት ያሰከረው የሰው ልጆች የዘመን መለወጫ

ነዋል አቡበከር

#ሳይ-ቴክ

ፎቶግራፈር በማርስ ላይ?

ሰዓለም ክንፈ

“ ቅንነት ድል ያደርጋል ”

ማውጫ



04 ርዕሰ አንቀጽ

05 ሀገር እንቁ ጣጣሽ
ያሳር ክንድሽ አቅፎን !
በሀይሉ ወ/ይፍራው

07 አራቱ በጎ ልማዶች
አብርሆት
በዶ/ር ቢኒያም ግርማቸው

08 የአውደብሩሀን ገጾች
ቆይታ
ከሀይለየሱስ ፈይሳ

13 የቅኖች ገጽ
የከፍታው ምስል
ብርቱ ሰው

15 ማን ነው? አትችይም ያለሽ?
ንንሳ አወት
አናናስ ግርማይ

16 ምቶት ያሰከረው የሰው ልጆች
የዘመን መለወጫ
አጃዒብ
ነዋል አቡበከር

18 እንደገና እንዳትሳሳቱ . . .
ቅምሻ

20 የማይታይ ቁስል
የአዕምሮ ጤና
ፍራኦል መስፍን

26 የቴዲ አፍሮና የጂጂ
ኢትዮጵያና አደዋ በወፍ በረር
ጥበባት
ጉቺ ሽመልስ

27 የመፅሀፍት ጥቆማ
እልፍ ገጾች
ዮናስ ኀ/ማርቆስ

30 ፎቶግራፈር በማርስ ላይ?
ማርስ ላይ ፎቶግራፈር?
ሳይ-ቴክ
ለዓለም ከንፈ

34 የቤሰብ ወግ
ጸሐፊ ሁሴን ይመር

መጽሔቷን ለማግኘት
እዚህ ይጫኑ



⊙አዘጋጅ ነዋል አቡበከር
e-mail-newalabubeker13@gmail.com
Telegram- @entisar13
(+251)937683378 ✆

⊙ማኔጂንግ ዳይሬክተር-ኤርሚያስ ደጀኔ
e-mail- ermiyasdejene@gmail.com
Telegram-@jeremy00
(+251)912178520 ✆

⊙አርታኢ - አወት ሀይለስላሴ
e-mail- awoth12@gmail.com
Telegram- @Awicha12
✆(+251)920152581

⊙አዘጋጅ በሀይሉ ወ/ይፍራው(መባ)
e-mail- ethiomebreku
3000@gmail.com
Telegram- @Dasolo
✆(+251)924140293

⊙አርት ዳይሬክተር-ፍራኦል መስፍን
firaolmesfin8@gmail.com
Telegram- @forgiven247
✆(+251)923602445

⊙ማርኬቲንግ - ዮናስ ኃ/ማርቆስ
e-mail- lijyoha2@gmail.com
Telegram- @Yonas_H
✆(+251)970514616

⊙ም/አዘጋጅ ነፃነት ጌታቸው
e-mail- netsanetg43@gmail.com
Telegram- @mistretigist
✆(+251)953498678

⊙ማርኬቲንግ - ያሬድ ለማ
e-mail-Yaredlemma487@gmail.com
Telegram- @Yared4444
✆(+251)932540523

⊙ከቨር ኢሉስትሬሽን & ሌይ አውት ዲዛይነር
ትንሳኤ አወል
e-mail- TensuAwel46@gmail.com
Telegram- @EsruMH
✆(+251)920019699

“ቅንዶክ | ቅንነት ዶክ ያደርጋል”

ቅንደል ዲጂታል መፅሔት በቅንደል ኢትዮጵያ የበጎ አድራጎት ማህበር ወጣቶች ተዘጋጅቶ በ E-square አድቨርታይዚንግ እና ኢቨንትስ የሚቀርብ በማህበራዊ፣ ስነ-ልቦናዊ እና ጤና ነክ ጉዳዮች ዙርያ የሚያተኩር ዲጂታል መፅሔት ነው።
የካቲት 2011 ተቋቋመ።

አድራሻ
(+251)912178520
(+251)920019699

e-mail- kdigitalmagazine@gmail.com
Telegram- @KenDelM
FaceBook- ቅንደል ዲጂታል መፅሔት
Www.Ethiokindel.com

የሁሉንም ትኩረት የሚሻው የኑሮ ውድነት

በሀገራችን ረጅምና አስቸጋሪ ግዜ ከወሰዱ የተለያዩ ፖለቲካዊ ለውጦች ጋር ተያይዞ የመንግስትም ሆነ የአብዛኛው ማህበረሰብ አትኩሮት ወደ ፖለቲካው ከሆነ ሰነባብቷል። ምንም እንኳን ፖለቲካው ከኢኮኖሚም ሆነ ከማህበረሰባዊ ትስስር ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ቢኖረውም የዕለት ተዕለት እሳቤና ድርጊታችንን በገዛው ፖለቲካ ሳቢያ ችላ እየተባለ ያለው ኢኮኖሚ አሳሳቢ ጀረጃ ላይ መድረሱን ብዙዎች ይስማሙበታል።

ኢትዮጲያ ውስጥ በከተማ ብቻ ያለው ስራ አጥነት 30 ከመቶ ደርሷል። የህብረተሰቡ የመግዛት አቅም እና የገበያው ሁኔታ እርቀቱ ያልተመጣጠነ መሆኑን ማህበረሰቡ በማማረር መግለፅ ከጀመረ ውሎ አድሯል። በኢትዮጲያ ውስጥ የዋጋ ንረት እያሻቀበ መሄዱ የአደባባይ ሀቅ ሆኗል። ወጣቱ በስራ አጥነትና ኢኮኖሚያዊ ልሽቀት ውስጥ መግባቱ ሀገሪቷ ካለችበት ችግር በተጨማሪ ሌላ እራስ ምታትን የሚፈጥር ነው። ምንም እንኳን እኩልነት የሰፈነበት አካታች ፖለቲካ ወይም ፖሊሲ ከመንግስት የሚጠበቅ ወሳኝ ኩነት ቢሆንም ማህበረሰቡ በተለይም ወጣቱ የፖለቲካ ተሳትፎውን እውቀት ላይ በተመረኮዙና በተመጣጠኑ ተሳትፎዎች ላይ ብቻ በማድረግ የንግድ ፈጠራና የስራ ጥራት ላይ የበለጠ ማተኮር ይኖርበታል።

ኢኮኖሚው ትኩረት ይገባዋል። ወጣቱ የስራ መፍጠር አቅሙ ሊዳብር ይገባል። በገንዘብም ሆነ ቀላልና ምቹ በሆኑ አሰራሮች መታገዝ እና መስራት አለበት። ህብረተሰቡ የሚታመምበት የዋጋ ንረት ጥያቄ ጆሮ ሊያገኝ ይገባል። በኢኮኖሚ እራሷን ያላደበረች ሀገር ሁሌም በልመና ውስጥ ናት። የተቀረው ፖለቲካም ሆነ ሉአላዊነት በዚሁ ይፈተናል። እያንዳንዱ ዜጋ ሰርቶ ለማደር ፣ ቆጥቦ ለመለወጥ ካልጣረ ለችግሩ መፍትሄ ማግኘት አይቻልም።

ምንም እንኳን መንግስት ስራ ለመፍጠርና ኢኮኖሚውን ለማረጋጋት ጅምር ስራዎችን እየሰራ ቢሆንም የወጣቱን ሰርቶ የማደግ ፣ በልቶ የማደር መሰረታዊ ጥያቄ የፖለቲካው ሹኩቻ በሚያወጣው የጎላ ድምፅ መዋጥ የለበትም። ማህበረሰቡ አሁን ላይ እየፈተነው ያለውን የኑሮ ውድነት የምንገራበት መንገድ ካላበጀን ፣ የዋጋ ንረቱን ካልገታን ፣ ወሰን የለሽ የነጋዴዎችን ፍትህ አልባ የንግድ ስግብግብነት ካላስቆምንና መንግስት እንደመንግስት ኢኮኖሚያዊ ተቋሟቱ ላይ ትኩረት አድሮጎ የፖለቲካ ወጣ ገባው የማይጎረብጣቸውና መልሰው ህዝቡን የማይጎረብጡ ተቋሟት መፍጠር ካልተቻለ ከፖለቲካው ባልተናነሰ ከባድ የኢኮኖሚ ፈተና ውስጥ መግባታችን ስለማይቀር መንግስትሞ ሆነ ማህበረሰቡ እንዲሁም ወጣቱ ኢኮኖሚው የሚገባውን አትኩሮትና ጥረት ሊሰጠው ይገባል።

በሀይሉ ወ/ይፍራው (መባ)
በድሬዳዋ ዩኒቨርስቲ የማኔጅመንት
መምህርና ቢዝነስ ሪሰርቸር
ethiomebreku3000@gmail.com

ሀገር እንቁ ጣጣሽ ያሳር ክንድሽ አቅፎን !

አዲስ አመት ገባ እንዲህ እንደዋዛ
ተፈጥሮ በውበት መንፈሴን ሳዩገዛ
ግን
አዲስ ተስፋ ነው ዘመን የልተኖረ
ከአሰለፍነው በላዩ በተስፋ የከበረ ፡፡

ጊዜ እንደ ሀሳብ መስመር ለሰው ልጆች በቁጥር ተሰፍሮ የተሰጠ የመኖር ተስፋ ፣ የነገን ህይወት የትናንትን አሻራ የያዘ የዘመን ሀዲድ ላይ የተሰራ የተፈጥሮ ስጦታ ነው፡፡ የግዜ አቆጣጠር የሰው ልጅ ተፈጥሮን ከማስተዋልና አጠቃላይ የጨረቃን ፣ የምድርን ፣ የፀሀይን እና የከዋክብት ቁርኝት በጥብቅ በመከታተል የቀመረው ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ የሰው ልጅ በዙሪያው ያሉት የህዋ አካላትና የተፈጥሮ ወቅቶችን በመደበኛነት መቀያየር ተከተሎ የግዜ ቀመርን መበየን ችሏል፡፡ ይህም የጨረቃን እንቅስቃሴ እንደዚሁም የምድርን ዙረት ተከትሎ የጀንበርን መጥለቅና መውጣት በጥልቀት ከማስተዋል የመነጨ ነው፡፡ ሰዓታትን ወደ ቀናት ቀናትን ወደ ወራት ከዚያም ወደ አመታት አስልቶ በመቀመር የግዜ አቆጣጠርን መፍጠር ችሏል፡፡ በዚህም መሰረት በአለም ላይ የጨረቃን ዙረት በመከተል የተቀመረ የግዜ አቆጣጠር (lunae calendar) በመባል የሚታወቅ ሲሆን ሌላኛው የምድርን በፀሐይ ዙሪያ መሽከርከር ተከትሎ የተቀመረው የፀሐይ የግዜ አቆጣጠር (solar calendar) በመባል ሲጠራ ሶስተኛው ቀመር እነዚህን ሁለት የግዜ አቆጣጠር አጣምሮ የተገኘው (lunesolar calendar) በመባል ይታወቃል ፡፡

ሰላም ውድ የቅንድል ዲጂታል መጽሔት ቤተሰቦችና የሀገሬ አምድ አንባብያን እንዴት ቆያችሁን? ሳምንታቶቹ በስኬት ወሩ በውጤት የታጀበና የሚታል ስራ የሚጨበጥ ውጤት እንዳገኛችሁበት ተስፋ አለኝ፡፡ በአዲስ አመት ልዩ ዕትም በሀገሬ አምድ ስለ ልዩ የሀገራችን ዘመን አቆጣጠር እና በእንቁ ተውቦ በጣጣ ታጅቦ በተስፋና በስጋት ፣ በፍርሀትና በምኞት ላይ ሆነን የምንቀበለውን አዲስ አመት ከተስፋችን ጋር በማያያዝ ላነሳ ወደድኩ፡፡ አለም ላይ የራሳቸው የዘመን አቆጣጠር ያላቸው ሀገራት ፣ ብሔሮችና ጎሳዎች ያሉ ቢሆንም በዋነኝት አለም የሚያውቃቸው አራት እንደሆኑ በተለያዩ የሐይማትና የታሪክ መዛግብት ተጽፎ ይገኛሉ፡፡ እነሱም፡- የጎርጎሮሳውያን የዘመን አቆጣጠር ፣ የአይሁዳውያን የዘመን አቆጣጠር ፣ የአረቦች ዘመን አቆጣጠር እንዲሁም የሀገራችን የኢትዮጲያ ዘመን አቆጣጠር የሚጠቀስ ነው፡፡ እነዚህ በዋነኝነት በዓለም ሀገራት ይታወቁ እንጂ በአንድ ሀገር ውስጥ እንኳን በርካታ ጎሳዎች የተለያዩ የዘመን አቆጣጠር አላቸው፡፡ ለምሳሌ በሀገራችን የሲዳማ ብሄር የዘመን መለወጫ ፍቼ ጨምበላላ ፣ የወላይታ ጊፋታ እና ሌሎችም ተጠቃሽ ናቸው፡፡ የአራቱም ዘመን አቆጣጠር አመጣጥና ይዘት በተመለከተ በቅንድል ዲጂታል መጽሄት የ2014 ዓ.ም የበዓል ልዩ ዕትም በሀገሬ አምድ ላይ በስፋት ለመዳሰስ ሞክረናል፡፡ አዲስ አመት በኛ በኢትዮጲያውያን ከአመት በዓልነት የዘለለ ጥልቅና ሰፊ ትርጉም አለው፡፡ ሀገራችን ኢትዮጲያ የራሷ የዘመን ቀመር አቆጣጠር ያላት ከመሆኗም በላይ በአለም የራሷን ምስልና ክብር ያኖረች የ13 ወር ጸጋ የታደለች ሀገር ናት፡፡

እንቁ-ጣጣሽ እንቁ የሆነ አዲስ ተስፋን ፤ አዲስ ህሊና ፤ ያልተኖረ አመትን የሚሰጠን ከበዓላት ሁሉ እጅግ የላቀው በዓል ነው፡፡ አዲስ አመት በሀገራችን ጅራፍ ከሚጮህበትና ሙልሙል ዳቦ ከሚቆረስበት የቡሄ በዓል ጀምሮ አሸንዳ፣ ሻደይ ፤ አሸንድዬና ሶለልን በሰሜኑ የሀገራችን ክፍል ልጃገረዶች ጨዋታ አጅቦ በመስከረም ወር በፈካው አደይ አበባ ደምቆ የሚገባ ብሩህ ወር ነው፡፡ ከጭጋጋማው ፤ ብርዳማው ፤ የጤዛና የጭቃ ወራት ወደ ፈካው የፀሀይ ፤ የብሩህ ደመና ስንቅ ወደ ያዘው የመስከረም ወር የምንሸጋገርበት የተስፋ አመት ባለቤቶች ብንሆንም ዳሩ ግን ዛሬም እንደ ሀገር ነጭ ለብሰን የምንቀበለው አዲስ አመት ሳይሆን በየሜዳው ያልበረዱ ባሩዶች ፤ በአደይ ፋንታ የወጣቶች ደምና ስጋ የተዘረጋት መሬት፣ ትናንት በአሸንዳ የቦረቁ እንስቶች ዛሬ በሰቀቀን ከሞቀው ጎጇቸው ወጥተው በጎዳና ላይ ተጠልለው ይገኛሉ፡፡ ዛሬ ላይ እንደ ትናንቱ ገበሬው ዝናብ እየደበደበው ለም መሬቱን ከማረስ ይልቅ ዘመንን ባልዋጀ ትርጉም የለሽ ጸብ ጠመንጃ አንግቶ ተራራ ላይ ነው፤ ዛሬ ለበዓሉ ድምቀት የሚሆኑ በሬዎችና ፍየሎች በበርሀ ላለው ወጥቶ-አደር (ወታደር) የዕለት ጉርስነት ይላካሉ ፤ ከሰው አልፎ እንስሳትን ያዘመትንበት የአንድ እናት ልጆች ጸብ ለራሳቸው ምቾት ብቻ በሚጨነቁ ግለሰቦች አማካኝነት የነገ ተስፋቸውንና ምኞታቸውን ሰውተው በየበረሀው የሚወድቁ ወጣቶችን ያሳየናል፡፡ አመት ቆጥረን በደልን መሻር ያቃተን ደካሞች ሆነናል ፤ ለይቅርታ የሚዘረጋ የማርያም ጣታችንን የጠመንጃ ቃታ እየሳብንበት ነው ፤ ትናንት ሻደይ፣ አሸንዳንና ሶለልን በጋራ ያከበሩ የሰሜን ልጃገረዶች ዛሬ ተከፋፍለው በቁጤማ ፋንታ ጥይት በጀርባቸው አንግተው ከደስታ ይልቅ የሀዘን ሲቃ ይጋታሉ፡፡ ደመናው ሽሽቶ ጸሀይ የምትወጣበት አደይ የምትፈካበት ወር እንደትናት የምንቦርቅበት ሳይሆን አንገት የምንደፋበት ነው፡፡ ዘመን ሲለወጥ መለወጥ ያቀታን ለምን ይሆን? ምድር ግዜ ጠብቆ ጭቃውን ደረቅ ክረምቱን በጋ ሲያደርገው የኛስ ልብ ክፋትን በይቅርታ ፤ ጥላቻን በፍቅር ፤ ጦርነትን በሰላም ፤ ጠብመንጃን በቁጤማ መለወጥ እንዴት አቃተው? ከአለም የተለየነው በዘመን አቆጣጠር ወይስ ተከባብሮና ተዋዶ የመኖር የራስ ባህል ጌጥ ማሳያ ፤ ታላላቅ አክባሪ ህዝቦች ብዙ ቀለም አንድ መልክ ያለን መሆናችን ነውን? አዎ አመት ከመሻገር በዘለለ የምንመልሰው እልፍ ጥያቄ አለ ፤ በዓል ደርሶ ከምንቀይረው ልብስ ውጪ ልባችንን በቅንነት ኑሯችንን በምክንያታዊነት ዘመናችንን ሀገር ፍቅር አንጻን ልቀይር ይገባል፡፡ አውዳመት አውዳሚ ከሆነው ትርጉም የለሽ ጸብ የምንርቅበት ሊሆን ግድ ይላል፡፡ ቃታ የሳቡ እጆች ልባቸውን ለእርቅ እጃቸውን ለሰላም ይዘረጉ ዘንድ ሀገሬ ትጣራለች፡፡ ለአዲስ አመት አዲስ ለብሰን ፤ ተስፋ ሰንቀን ፤ ፍቅር አኑረን ፤ መልካምነትን ተግብረን የምናከብረው ብቻ ሳይሆን አዲስ ስንለብስ ካለን ላይ ለተቸገሩት የምናካፍልበት ፤ በፍካት ስንስቅ በአዕምሯችን የተሞላውን ክፋት ፤ ዘረኝነት ፤ ጥላቻ ፤ ቂም ወደ ኋላ ጥለን እኛ ሞልቶ ተርፎን ጠግበን ስንደፋ ምንም የሚቀመስ ላላገኙ በየጎዳናው የወደቁትን የምናስብበት ዘመን ፤ የሀሳብ ፤ የኑሮ ፤ የትምህርት ፤ የህይወት መንገድ ለውጥ የምናደርግበት አመት መሆን ይገባዋል፡፡ ውድ የሀገሬ አምድ አንባቢያንና የቅንድል ዲጂታል መጽሔት ቤተሰቦች በትናንት ቁርሾ ፤ በደል ፤ ቂም የነገን ብርሀን የምንቀበልበት ሳይሆን በፍቅር ፤ በአንድነት ፤ በመቻል ፤ በቅንነትና በህብረት የምንመራረቅበት ይሁንልን፡፡ አዎ አሜን እያልን ሀገርን ፤ አሜን እያልን እማማን ፤ አሜን እያልን ጋሼን ፤ አሜን እያልን እታለምን ፤ አሜን እያልን የሰው ልጅን ሁሉ የምንመርቅበት እንዲሆን በምርቃት መጪውን ግዜ እንቀበል፡፡ ተቀበይ ሀገሬ ተራሮችሽ በአደይ ፤ ልጆችሽ በጸጋ ፤ መንደርሽ በደስታ የሚበሩበት አመት ያምጣልሽ ቃታ የሳቡ እጆች የማሪያም ጣታቸውን ለይቅርታ ይዘርጉልሽ ለጸብየምንዝርበት ሳይሆን ለሰላም የምጮህበት አንደት ለህዝቦችሽ ያድል፡፡ አሜን በይ ሀገሬ ምድርሽን ከአደይ የበለጠ ምን አይነት አበባ ሊወክላት ይችላል? ከመስከረም የበለጠ ወርስ ምን አለሽ ? በቢጫ ቀለም የያዘች ውብ አርንጓዴ ምድርሽን በቀይ ደም ተቦክቶ በተቀበረ መሬት የበቀሉ ልዩ ስጦታዎችሽ ናቸውና አሜን በይ ሀገሬ፡፡ ውድ አንባያን መጪውን አመት በመተሳሰብ ፤ በመዋደድ ፤ በቅንነት ፤ በምክንያታዊነት ፤ በሀገር ፍቅር ደምቀን ራሳችንን ፤ቤተሰባችንን ብሎም ሀገራችንን ኢትዮጲያ ወደ ሰላም የምናደርስበት ዘመን ያድርግልን እያልኩ የአዲስ አመት የሀገሬ አምድ ጽሁፌን አበቃሁ፡፡

መልካም በዓል!

እንደ ምድሩ የፈካ ፤ እንደ ወራቱ ያበራ የሰላም ዘመን ያድርግልን!
ኢትዮጲያ ለዘላለም በህዝቦቿ ፍቅር ትኑር...

አራቱ በጎ ልማዶች

በማህበራዊ ግንኙነታችን ለሠዎች ምቹ ፀባይ ኖሮን በነፃነትና በግልፅነት የተሞላ ጤናማ ሕይወት መኖር እንድንችል ከሚረዱን ክህሎቶች መካከል የሚከተሉት ተጠቃሽ ናቸው::

ቅንነት

በየቀኑ ልናከናውናቸው ከሚገቡና ማኅበራዊ ሕይወታችንን ለማሳደግ ከሚረዱን ተግባራት መካከል በቅንነት ስሜት ተሞልተን ሌሎችን መርዳት የመጀመሪያው በጎ ልማድ ነው::ለምሳሌ ከተሣፈርንበት ታክሲ ስንወርድ ከፊታችን ለምትገኘው የልጆች እናት ቅድሚያ መስጠት፣ካፍቴሪያ ገብተን አገልግሎት ለምትሰጠን አስተናጋጅ በትህትና እና በፈገግታ የታገዘ ትዕዛዝ መስጠት ግንኙነታችንን ጤናማ ያደርገዋል::በሠጠነው ነገር ልክ ከሌሎች ተገቢውን መልስ ባናገኝ እንኳን ትልቁ ቁም ነገር በየዕለቱ አንድ ሰው መርዳት ወይም ደስታ እንዲሰማው ማድረግ መቻላችን ነው::እንዲህ አይነቱን ልማድ ስናዳብር በየዕለቱ በየትኛውም ሰው ሕይወት ላይ ተፅዕኖ መፍጠራችን ብቻ ሳይሆን በቀላሉ ከማንም ጋር ተግባቢና ለሌሎች ምቹ የሆነ ስብዕና ይኖረናል::እያንዳንዱን ሰው በፈገግታ ተሞልተን በቀረብነው መጠም ማንነቱን በግልፅ ለማሳየት ፈቃደኛ ሊሆን ስለሚችል ከድክመትና ጥንካሬው የምንማርባቸውን አጋጣሚዎችም እናገኛለን::

አመስጋኝነት

እያንዳንዱ ሰው ከተፈጥሮ በየጊዜው ለሚያገኛቸው በጎ ሥጦታዎች ለፈጣሪው ምስጋና ማቅረቡ የተለመደ ነው::በሰዎች ዘንድ እርስ በእርስ የመመሥጋገኑ ልማድ ግን በሚፈልገው መጠን የዳበረ አይመስልም በዕለታዊ እንቅስቃሴዎቻችን ስለ እኛ የሚጨነቁ መልካሙን ሁሉ የሚመኙልንና በጉብዝናችንም ወቅት አድናቆታቸውን የሚቸሩና በርካታ ሰዎች በዙሪያችን ይኖራሉ::እነኚህን ሰዎች ልናመሰግናቸው ይገባል::ምስጋና በቸርናቸው መጠን ግንኙነታችን እየጠነከረ ከመምጣቱ በተጨማሪ በውስጣችን ያለውን አዎንታዊ ስሜት የማሳደግ አቅም እናገኛለን:: ከቤተሰባችን አባላት ከሥራ አጋሮቻችን ወይም በሆነ አጋጣሚ ከምናገኛቸው አዳዲስ ሰዎች ለሚደረግልን ድጋፍ ተገቢውን ምስጋና ከሠጠን ይህ በጎ ልማድ ተጨማሪ የሕይወት አጋዦች ማግኘት የምንችልበት ሌላ የግንኙነት በር ይከፍትልናል::

ራሳችንን መውደድ

ራሳችንን በወደድንና በተቀበልን መጠን ለምናከናውናቸው ድርጊቶች ሁሉ የሌሎችን ይሁንታ ወይም ድጋፍ ለመጠበቅ መገደዳችንን ይቀራል::ራሳችንን መቀበል መቻል በራስ መተማመናችንን የሚያሳድግ በመሆኑ ሃሳባችንን ለሌሎች ማጋራት ካስፈለገን እንኳን ምንም አይነት ፍርሃት አይሰማንም ለራሳችን መወደድ ሲጨምር የልባችንን መጋረጃ ገልጠን በሰዎች ፊት ብርሃናችን እንዲያበራና የተለየ ስብዕና እንዲኖረን በማድረግ እንሞክራለን::ይህ ደግሞ በዙሪያችን ያሉ ሰዎች በስብዕናችን እንዲሳቡና ምክንያት ይሆናል::ራሳችንን በተገቢ መንገድ መወደድ ስንጀምር ተገቢውን ዋጋ ሊነፍጉን ከሚሹ ሰዎች በመራቅ በአስተሳሰብ በአመለካከት ከሚመስሉን ደስተኛና አዎንታዊ ሰዎች ጋር ያለንን ግንኙነት እናሳድጋለን:: (በዚህ ርዕስ ስር የተገለፀው ራስን መውደድ ሌሎችን ለመጉዳት ጥቅም ላይ ከሚውለው የራስ ወዳድነት ስሜት የተለየ መሆኑን ማስተዋል ተገቢ ነው::)

ይቅር ባይነት

ከሰዎች ጋር ለመኖር እጅግ ጠቃሚ ከሆኑ ክህሎቶች መካከል አንዱ ይቅር ባይነት ነው::ሰዎች በማወቅም ይሁን ባለማወቅ ስሜታችንን የሚጎዱ ወይም ጥቅማችንን የሚያስቀሩ ድርጊቶች ሊፈፅሙብን ይችላሉ::እያንዳንዱን ድርጊት በአሉታዊ መንገድ ብቻ በመቀበል ግንኙነታችንን ከማቋረጥ ይልቅ በይቅር ባይነት ማለፍ የትልቅነት ምልክት ነው::

ምንጭ- ሰው ሁን ከሰውም ሰው ሁን የትስስር ገፅ የተወሰደ

የ አውደብሩሀን ገጾች

ሰላም የተከበራችሁ እና የተወደዳችሁ የቅንነት ዘማሪ ፣ የምክንያታዊነት ምልክት ፣ የሀገር ፍቅር ማሳያ የሆናችሁ ባለራዕይ የቅንድል ዲጂታል መጽሄት አንባቢያን፡፡ እንደሚታወቀው በአውደ ብሩኃን ገጻችን በሀገራችን ኢትዮጲያ በኪነ-ጥበብ ፣ በትምህርት ፣ በጤና ፣ በማህበራዊ ግልጋሎት ፣ በበጎ አድራጎት ፣ በስፖርትና በሌሎች የተለያዩ የሙያ ዘርፎች ለሀገራቸው በርካታ ትሩፋትን ያበረከቱና ቅንነትን መለያቸው ፣ ምክንያታዊነትን የህይወት መርህ አድርገው በሀገር ፍቅር ከተቃኙ መካከል ለእናንተ ለአንባብያን በተለይም ለወጣቶችና ለሴቶች ከህይወታቸው ፣ ከስብዕናቸው ፣ ከስራ ውጣ ውረዳቸውና ከትዝብታቸው ትማሩበታላችሁ ያልናቸውን ወደእናንተ የምናደርስበት አምድ ነው፡ ፡ ታዲያ በዛሬው የዐውደ ብሩኃን ገጽ እንግዳችን ድምፃዊ ሀይለየሱስ ፈይሳ ነው፡፡ ሀይለየሱስ ፈይሳ ከጥበብ ትርፋቱ ፣ ከህይወት ልምዱ ሊያካፍለን ከነፃነት ጌታቸው ጋር ቆይታ አድርጓል፡፡ እንድትከታተሉን አስቀድመን በትህትና እንጠይቃለን፡፡

ቅንድል በመጀመሪያ ሀሳባችንን ተረድተህና ደግፈህ ቅንነግ በሚሰበክበትና ስኬታማ ሰዎች ልምዳቸውን በሚያካፍሉበት መፅሔታችን እንግዳ ለመሆን ፍቃደኛ ስለሆንክ በቅንድል መፅሔት አዘጋጆችና በውድ አንባቢዎቻችን ስም ከልብ አመሰግናለሁ፡፡

ሀይለየሱስ በእውነት እናንተም እንግዳችሁ እንድሆን ስለመረጣችሁኝ እጅግ በጣም አመሰግናለሁ፡፡ እግዚሐብሄር ያክብርልኝ፡፡

ቅንድል እንደው ወደዋናው ጥያቄዎቻችን ከማለፋችን በፊት ለአንባብያን እራስህን ብታስተዋውቅልን? ሀይለየሱስ የት ተወለደ ? የት አደገ? ልጅነትህ ምን ይመስል ነበር? አንተ ባደክበት አከባቢ አንድነታቸው ፍቅራቸው በደጋገፋቸውን እግረ መንገድህን አስታውሰህ ብታጫውተንም ደስ ይለናል፡፡

ሀይለየሱስ ድምፃዊ ሀይለየሱስ ፈይሳ እባላለሁኝ፡፡ ከሙዚቀኛነት ባለፈ የግጥምና የዜማ ደራሲም ነኝ፡፡ የተወለድኩት ደሴ አከባቢ ነው፡፡ ያደኩት ግን እዚሁ አዲስ አበባ ነው፡፡ እንግዲህ ብዙዎቻችን ያደግንበት ማህበረሰብ የመጀመሪያ ትምህርት ቤታችን ነው፡፡ ለደስታ ለሀዘንም በመጠራራት ከልዩነታችን ይልቅ አንድነታችን ላይ እንድንበረታ ፣ የጎረቤትን ችግር እንደራስ በመቁጠር ህመም ፈጣሪዎች ሳይሆን ህመም ተጋሪዎች እንድንሆን ፣ መከባበርን እና መዋደድን ከጥላቻ ብዙ እጥፋ አብልጠው ያስተማሩን ናቸው፡፡ እኔ የማውቀው ያደኩበት ማህበረሰብ እንደዚህ ነበር ፡፡ ልጅነቴም ሁላችንም ልጅነታችንን በምናሳልፍበት መንገድ ነው ያሳለፍኩት አንደኛ ደረጃ ትምህርቴን ,,,,,,ተማርኩ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርቴን ደግሞ አዲስ ከተማ ነው የተማርኩት እንደዚህ እንደዚህ እያለ እየተኖረ ነው እንግዲህ፡፡

ቅንድል መጀመሪያ ወደ ሙዚቃው ኢንዱስትሪ የገባህበት አጋጣሚ እንዴት ነበር? ስራህና የአድማጮች አቀባበልስ እንደጠበከው ሆኖልህ ነበር?

ሀይለየሱስ እምምምም በእውነት ወደ ሙዚቃ የገባሁበትን ትክክለኛ አጋጣሚ በትክክል አላስታውስም፡፡ ግን ከልጅነቴ ጀምሮ በተማርኩባቸው ትምህርት ቤቶች እዘፍን እንደነበር አስታውሳለሁ ከዛ ትምህርቴን እንደጨረስኩ ወደ ሙዚቃው ስቀላቀል ግን እንደማንኛውም

ቀጥሎ ደግሞ ክለብ ስሰራ ብዙ ልምዶችን ስላገኘው ቀጥታ ሙዚቃዎቼን ሪኮርድ ወደማድረጉ ገባሁ ማለት ነው:: የመጀመሪያ ስራዬ "አስኮቱ" እሱም በጣም ጥሩ አቀባበል ነበረው ፡ ከዛ ቀጥሎ ደግሞ "ሳላይሽ" ን ሰራሁ አቀባበሉም ጥሩ ሆነ እግዚሐብሄር ይመስገን በስራዎቼ ሁሉ ደስተኛ ነኝ:: •

ቅንድል ሀይሌ የመምህር ልጅ ነው ታድያ የመምህር ልጅ መሆነህ የተለየ የጠቀመህ ነገር አለ በህይወትህ?

ሀይለየሱስ አዎ የመምህር ልጅ ነኝ:: በርግጥ ሁሉም ቤተሰብ መምህር ባይሆንም ለልጁ የሚሰጠው የሚጠቅም ነገር ይኖረዋል ነገር ግን የመምህር ልጅ በመሆኔ የተሻለ ነገር ይገኘ ወጣሁ የምለው የማንበብ ልምድን ነው:: ለኔ ማንበቤ ብዙ ጠቅሞኛል ከምነግርሽ በላይ አባቴ የአሁን ማንነቴ ላይ እንድደርስ በደንብ ለፍቶብኛል::

ቅንድል "የአዲስ ቀን ፀሀይ" አልበም ለመስራት ከነበረው ችግር በላይ ለህዝብ ለማቅረብ ብዙ ነገሮችን እንዳለፈ በብዙ ቃለ መጠይቆች ገልፃል የነበረውን ነገር በጥቂቱ አውራን እስቲ? እንዲሁ ህዝብ ጋር የነበረውን አቀባበልም እንዴት ነበር የልፋትህን ያህል አግኝተሃል ?

ሀይለየሱስ እእእ እውነት ለመናገር አዎ ብዙ ውጣ ውረዶች ነበሩ ግን ያው ሰርቶ ስለማቅረብ ስናወራ ብዙ እንቅፋቶች እንደሚኖሩት ግልፅ ነው:: አልበም ስትሰራ ደግሞ እንዴት ሊከብድ እንደሚችል መገመት ቀላል ነው:: ለኔ በወቅቱ ዘፈኑን ሰርቼ ህዝቡ ጋር ለማድረስ ብዙ ውጣ ወረዶችን አልፌያለሁ ግን አሁን ስሰማው እንኳን ሆነ እንኳን ለፋሁበት ነው የምለው:: ስለአቀባበሉ ስናወራ ደግሞ የልፋት ያህል ብለሽ መጠን የምታስቀምጭለት ነገር አይደለም ፡ በተመሳሳይ የደስታ መጠን ብለሽም ገደብ ልታበጂለት አትችይም ግን በጠበኩበት መጠን ሳይሆን እኔ እንድሰራው ፈልጌ ወደመሬት አውርጄ የሰራሁት ነገር ለህዝብ ደርሶ እኔ ራሱ ስሰማው ያለመሰልቸቴ ሰዎች ሲሰሙት ሳይ እረካለሁ ያ ነው የኔ ትርፍ የማልፀፀትበትን ነገር መስራት መቻሌ::

ቅንድል አርያዬ ነው የምትለው ሰው አለህ? ምክኒያትህስ?

ሀይለየሱስ አባቴ ለኔ አርያዬ ነው:: እኔ አሁን ባለሁበት እድሜ ሆኜ የሆነ ትልቅ ሀላፊነት ወስደህ በውስጥ የሚፈታተኑህን ችግሮች አልፈህ ፡ ቢከፋህ ቢጨንቅህ ብትቸገር የችግሮችህ ማለፊያ እንዲሆን ሌላ ነገር መስራት ስትችል ይሄን ከማን ተምሬው ነው ትያለሽ አይደል? እኔ ከአባቴ ነው የተማርኩት ፡ አባቴ ያለ እናት ነው ያሳደገን ለሚፈጠሩት ፈተናዎች ሁሉ መፍትሄ የሚያደርጋቸው ነገሮች የሚደንቁ ነበሩ ፡ አንዱ ወደቤተክርስቲያን መሄድ እንደነበር አስታውሳለሁ:: እኔ አድጌ አሁን ስመለከተው እሱ በዛ ጊዜ ተቋቁሞ ያለፋቸው ነገሮችን ሳስባቸው ጀግና ይሆንብኛል:: አሁን ሰዎች ሲጨንቃቸው ወደሚያደርጉት አላስፈላጊ ነገሮች ውስጥ የመግባት ምርጫ ነበረው አባቴ ግን ምርጫውን ግን ወደዛ አላደረገም ሁሉን ፈተና አልፎ መልካሙን መንገድ መርጧል :: እና ለኔ አርያዬ እሱ ነው::

ቅንድል በዚህ በሙዚቃው ኢንዱስትሪ እንደማንኛውም ባለሞያ ከባዱ ነገር ምንድነው ትላለህ? አንተን ፈትኖህ የነበረ ነገር ካለም አካፍለን ለሌሎች እንዲሆን?

ሀይለየሱስ ሙዚቃ በጣም ከባድ ነገር አለው። በአምስት ደቂቃ ተከፍቶ እንደሚሰማው ቀላል ነገር አይደለም በጣም ከባድ ነው። ይቺ የአምስት ደቂቃዋን ዘፈን ለመስራት ብዙ ጉዜ ይፈጃል ብዙ አቅም ቀንዘብ ይጠይቃል። ከብዙ ልፋት በኋላ አልቃ ሰዎች የሚያዳምጧት የአምስት ደቂቃ ሙዚቃ ተከፍቶ እንደሚያልቀው አይነት አስተላለቅ አይደለም ተሰርታ ያለቀችው። ያምራል ተሳካለት ቆንጆ ዘፈን ሆነ የሚለው ግን በዛች ድካም ውስጥ ያለ ነገር ነው። እሯጮችን የሚለያቸው መጨረሻ ላይ ያለችዋ ደቂቃ አይደለች? በሙዚቃው አለምም ለፍተሽ ለፍተሽ መጨረሻውን ለማሳመር መጋጋጥ ግድ ይልሻልና እሱ ላይ በደንብ መስራት ይጠይቃል።

ቅንድል አሁን ሁላችንም እንደምናውቀው እንደሀገር የተጨነቅንበት ጊዜ ላይ ነን እንደው ይሄን ውጥንቅጥ ባሰብክ ጊዜ ምንድነው የሚሰማህ? የሙዚቀኛ ድርሻው ምንድነው ትላለህ? እንደዚህ ትውልድ አካል ምን ብናደርግ ብለህ ታስባለህ?

ሀይለየሱስ እምም ያው አሁን እየገጠሙን ያሉ መከራዎች ሁሉ የአዲስ ቀን ፀሀይ ነው ብዬ አስባለሁ ሊነጋ ሲል የሚጨልም አይነት ነገር ነው። ከዚህ ውጪ ግን ክፉና ደጉን መለየት በሚከብድበት ጊዜ ላይ ነን ያለነው ለዚህም መፍትሄው ፀሎት ነው መፀለይ አለብን። ከዛ በተረፈ ግን በነዚህ ጊዜዎች ላይ አንድ ሆኖ በፊት የነበረችውን ኢትዮጵያ እንደነበረች ለማቆየት በአሁኑ ሰዓት ላይ ትልቁ የሚያስፈልገው ነገር አንድነታችን ነው። በአንድነት የመዘመር ልምድ ያስፈልገናል። አርት በጣም ትልቅ መሳሪያ ነው ነገቆችን ለመለወጥ ስለአንድነት ቢዘመር ስለአንድነት ቢዘፈን ስለኢትዮጵያዊነት ቢዘፈን በዚህ ሰዓት ላይ አስፈላጊና ቦታውም ነው ብዬ አስባለሁ።

ቅንድል ሀይለየሱስ ሙዚቀኛ ባይሆን ምን ይሆን ነበር? ሰው የማያውቀው ሌላ የተለየ ተስጦ አለህ?

ሀይለየሱስ ሙዚቀኛ ባልሆን ኖሮ ጠበቃ እሆን ነበር ፡ አሁን ግን የጀመርኩትን መንገድ ነው የምጨርሰው።

ቅንድል ኢትዮጵያዊነት ማለት ላንተ ምን ማለት ነው? የሀገር ፍቅርስ?

ሀይለየሱስ ኢትዮጲያዊነት ለኔ? ማንነት ነዋ ደሜ ! የሀገር ፍቅር የሚገለፀው በቤተሰብ በአከባቢ በመዋደድ በመከባበር ነው። ሀገር የሚባለው ትልቅ ነው የሚጀምረውም ከቤት ነው ፡፡ የቤተሰቦቻችን ራስ እናቶቻችን ወይን አባቶቻችን የቢቶቻችን አለቆች ወይንም በሀገር ደረጃ እንደምንለው ጠቅላይ ሚኒስተሮች ናቸው እነሱ በሚያስተዳድሩት ቤት ላይ የአስተዳደር ችግር ካለ ያ ነገር አድጎ ሀገር ይጎዳል በተመሳሳይ አስተዳደጋቸው አይንም አስተዳደራቸው መልካም ከሆነ ሀገር ይሰራሉ ማለት ነው። የሀገር ፍቅር አጠገባችን ባለው ሰው ላይ በምናደርገው ነገር ይገለፃል። የሀገር ፍቅር በልባችን በምናስበው ጥሩና መልካም ነገርም ይመዘናል ከልብ የሚሰፋ የት አለ? ሀገራችንን የምንወድ ከሆነ ከራሳችን ነው መጀመር ያለብን ብዬ አስባለሁ።

ቅንድል በአዲሱ ዓመት ከሀይሌ ምን እንጠብቅ? አዳዲስ ስራዎች እጅህ ያሉ ይመስለኛል መች እንጠብቅ እነሱንስ? የፍቅር ንቅሳት ብለህ መጠሪያ የሰጠኸው አዲስ ነጠላ ዜማ ከሰሞኑ ልትለቅ ነው:: የፍቅር ንቅሳት ስትል ምን ማለትህ ነው?

ሀይለየሱስ በአዲሱ ዓመት እንግዲህ "የፍቅር ንቅሳት " አንዱ ነው:: በመንግስት ደረጃ የመጣ 28-ትራኮችን የያዘ ብዙ አርቲስቶች የተሳተፉበት አልበም በቅርቡ ይመረቃል:: እዛ ላይ "ሀገርና ሚስት" የሚለውን ግጥምና ዜማ በመስራት እንዲሁም አብሬ በመዝፈንም ተሳትፌያለሁ:: የፍቅር ንቅሳት ሀሳቡ ምን መሰለሽ ,,,,,እንግዲህ ስንኳዝ አብረን ተገጫጭተን ፣ ተገፋፍተን ፣ ተመታተን ፣ ተሰዳድበን ሊሆን ይችላል ነገር ግን ለነገ ለሚሆን ጥሩ ምኞት ያኛው የቆሰልነው የደማነው የተሰበርነውን ስብራታችንን የፍቅር ንቅሳት አድርገነው ወደፊት እንጓዝ የሚለውን የያዘ ነው::

ቅንድል ፦ አርቲስቶች ሰብሰብ ብላችሁ በጋራ አዲስ አልበም እንደሰራችሁ እየተነገረ ነው እስቲ ስለሱ አውራን? ያንተስ ተሳትፎ ምንድነው? ሰብሰብ ብሎ አልበም የመስራት ሀሳቡስ እንዴት መጣ?

ሀይለየሱስ ፦ አልበሙ በመንግስት ደረጃ የመጣ ነው አንድ አይነት ህብረትን ለመፍጠር በመፈለግ ፡ እና እኔም ሀሳቡ ሲነገረኝና እንድሳተፍ ስጠየቅ በደስታ ነው የተቀበልኩት ፡ ቅድም እንዳልኩሽ "ሀገርና ፍቅር " የሚለውን ግጥምና ዜማውን በማዘጋጀት አብረውኝ ከሚያዜሙ ጓደኞቼ ጋር ጥሩ አድርገን ሰርተነዋል ቀጣይ ሳምንት ይወጣል ብዬ አስባለሁ::

ቅንድል በመጨረሻ እኛ ቅንድሎች ቅን ምክኒያታዊ ሀገር ወዳድ ትውልድ ለኢትዮጵያ በሚል መሪ ቃል የተለያዩ መልካም ስራዎችን እየሰራን እንገኛለን:: በዚህ አጋጣሚ ለኛም ለወጣቶችም የምታስተላልፈው መልዕክት ካለ እድሉን ልስጥህ?

ሀይለየሱስ ፦ በዚህ ሰዓት ላይ እንግዲህ እንደወጣት በነገሮች ሁሉ ስሜታዊ ሳንሆን በተረጋጋ መንፈስ ለሚሰማውም ለሚታየውም ነገር ሙሉ የሆነ ግምት እየሰጡ ውሳኔዎችን ከመወሰን ተቆጥበን የምናደርጋቸውን ነገሮች ሁሉ በማስተዋል እና በመጠንቀቅ እናድርግ ለማለት እፈልጋለሁ:: እናንተም እየሰራችሁ ያላችሁት ነገር በቀላሉ የሚታይ አይደለም የሀገር ባለውለታ ናችሁ ለነገዋ ብረሃን እያቀበላችሁ ያላችሁት መልካም ነገር ትንሽ አይደለምና በርቱ ከጎናችሁ ነን::

ቅንድል ፦ እኔ ጨርሻለው ሀይሌ በድጋሚ የቅንድል ዲጂታል መፅሔት እንግዳችን ስለሆን ከልብ እናመሰግናለን::

ሀይለየሱስ ፦ እኔም አመሰግናለሁ::

እንኳን ለ2014 ዓመተ ምህረት በሰላም አደረሳችሁ ፤ አደረሰን!

በአሉን ስናከበር ቅንነትን በተግባር ፣ ምክንያታዊነትን በህይወት ፣ ሀገር ፍቅርን በመኖር በጉዟችን እናንግስ ። ሰላም ከኛ ይጀምሩልና ልባችን በሰላም ይፅና ፣ ኑጋችን በዕቅድ ይጀመር ፣ አብሮነታችን በፍቅር ይታደስ ፣ በሁሉም ዘርፍ እንክበር ፣ ተርፎን የምንቸር ብቻ ሳይሆን ካለን የምናካፍል ያድርገን ። እንደ ቀዬው በውብ ገፅ የፈካ ህይወት ፣ እንደ መስከረም ወር ብርሀን የሆነ ግዜ ፣ የጥላቻ ፍፃሜ ይስጠን ። ሀገራችን ከቢጫ ወርቅ የደመቀ ምንስ ውበት ኢኖራት ፣ በፀጋ የተሸለመ 13 ወር ተሰቶናልና በመታደስ ፣ በመፅናት ፣ በመታዘዝ ፣ በመባረክ እንኑረው ። ደስታ በቤታችን ሰላም በሀገራችን ፤ ፍቅርን ለሰው ልጆች ሁሉ ፈጣሪ እንዲሰጥልን የቅንደል ዲጂታል መፅሔት የዝግጅት ክፍል ይመኛል ፡ ፡

ቅን
ምክንያታዊ
ሀገር ወዳድ ትውልድ ለኢትዮጵያ!

#ቅንነትድልያደርጋል
ቅንደል ዲጂታል መፅሔት

ቅንደል ዲጅታል መጽሔት
kdigitalmagazine @gmail.com

የከፍታው ምስል ብርቱ ሰው



ዝና ፣ ሀብት ፣ ክብርና ሽልማት ጥሩ ትከሻና ህሊና የሌለው ሰው ሊሸከማቸው ብቻ የሚችል ብርቱ ሰው ነው። ጥንካራ ስራ ፣ ስነ-ምግባር ፣ ጥረትና ሀገር ፍቅር የሱ መለያ ናቸው። አይደለም ተከፍቶ ተደስቶም የሀገሩ ስም ሲጠራ እምባው ይቀድማል። በሀገረ ሆላንድ ከመከበር አልፎ እንደ ምሳሌ የሚጠራ ልዑል ነው ቢባል ማጋነን አይሆንም። በሱፍም በቁምጣም ስኬት እጁ ላይ ነች ለዚህ ደሞ ሚስጥሩ ስራ ወዳድነቱ ብቻ ሳይሆን ጥረትን ከስኬት ጋር መዝኖ መኖር የሚችል ብርቱና ልባም ሰው በመሆኑ ነው። ከ28 በላይ ሪከርዶችን በአለም መድረክ በኢትዮጲያ ስም የግሉ አድርጓል ፣ ከኦሎምፒክ መድረክ እስከ ግል ውድድሮች የማይዝሉት ጉልበቶቹ በአውሮፓ ጎዳናዎችና እስቴድየሞች ተመስክሮላቸዋል ፣ ከያንያንን ሳይቀር ያስደመሙ ጉልበቶች በአንድ ሌሊት ግጥምና ዜማ ተሰናድቶላቸው ለክብሩ ተሰጥተዋል። ይህ ሰው ሀይሌ ገ/ስላሴ እንደሆነ ማንም ይመሰክራል፡፡ እሱ በቢዝነሱም አለም በተለይ በሆቴልና ቱሪዝም ዘርፍ ለበርካታ ኢትዮጲያውያን የሰራ እድል መፍጠር የቻለ ባለ ብዙ ክብር ባለ ብዙ ስራ ባለቤት ነው። ቅንድል ዲጂታል መጽሄት በዛሬው የአዲስ አመት ልዩ ዕትም ይህን የሀገር ኩራት የቅኖች ምሳሌ ስትል ለሀገር የዋለውን ውለታ በማስታወስና አሁንድረስ ለብዙ ዜጎች በተለይም ለወጣቶች ምሳሌ ሊሆን የሚችል ስራ በመስራቱ ቅንነትን በስራውና በኑሮው ምክንያታዊነቱን በስራው ፣ ሀገር ፍቅሩን በተግባር ለኖረበት ባለ ውለታነቱ አመስግነናል። ደስታን ከሚናገረው ፈገግታውና ስኬቱ ጋር ለሀገር ብዙ ቀሪ ትሩፋት እንዲሰጥ አደራ እያልን እድሜና ጤና ተመኘን።

kendelM

የስብዕና ልዕልት

በሀገራችን ዝናን ለመልካም ስራ መጠቀም ክብርና እውቅናን ጠብቆ ለወጣች አርአያ መሆን እንደ ስያሜውም አርቲስት የህዝብ ልጅ የሚለውን የሚመጥኑ ጥቂቶች ናቸው። አርቲስት የህዝብ ልጅ ሚሆነው እውቅናውን ፣ ክብሩንና ማንነቱን ለሰጠው ህዝብ መልሶ በቅንነትና በምክንያታዊነት ማገልገል ሲችል ነው። በተለይም እንስት አርቲስቶቻችን ብዙ ተከታይ እንዳላቸው መጠን ምሳሌ የሚሆን ስራን ሲሰሩ መመለከት ከፍ ያለ ምስጋናና ክብር ሊያሠጣቸው ይገባል። በጉዲፈቻ ፊልም አድናቆትን አግኝታ በርካታ የመድረክና የፊልም ስራዎችን አቅርባለች። በተለይም በገመና ድራማ ላይ በነበራት ድንቅ ስራ ብዙዎች ልብ ውስጥ መግባት የቻለች ልባም ተዋናይ ናት። ዝነኝነትን ለመልካም ስራ ከማዋል በዘለለ በስነ ምግባርና በህይወት እንቅስቃሴዋ ለብዙ ሴት አርቲስቶችና ወጣቶች ምሳሌ ያረጋታል፡ ፡ በልብ ህመም ለሚሰቃዩ ወገኖች ከፊት ሆና በርካታ የበጎ አድራጎት ተግባራትን እየከወነች ነው። ልባም ሆና በልብ ህመም የሚሰቃዩ ህጻናትን ተስፋ እየመገበችና ድጋፍ እያሰባሰበች ብዙ ስራ ሰርታለች። አሷ በጎ አድራጎት ሲባል ቀዳሚ ፣ ቅንነት ሲባል ምልክት ፣ ክብርን ጠብቆ ምሳሌ መሆን ለሷ የሚገቡ መግለጫዎች ናቸው። አርቲስት መሰረት መብራቴ ብዙዎችን ወደ ኪነ-ጥበብ እንዲገቡ ሰርቶ መቻልን ያሳየችና ዝናን ክብርን ጠብቆ ማቆየትን ያወረሰች የቅኖች ምሳሌ ብለን በዛሬው ዕትማችን ልናመሰግናት ወደናል። መሰረት በቀጣይ በበርካታ ስራዎች መብራት እንደምትሆን እንተማመናለን ፤ ጤናና እድሜ ተመኘን።



አናናስ ግርማይ
የሥነ-ማህበረሰብ ባለሙያ
britanitam@gmail.com>

ማን ነው? አትችዪም ያለሽ?

የፆታ እኩልነት ሰብአዊ መብት ቢሆንም በአለም ያሉ ሴቶች በኢኮኖሚ ተሳትፎ፤ መሰረታዊና ከፍተኛ የትምህርት እድል፤ የፖለቲካ ውክልና፤ ጥሩ የጤና አገልግሎት እና ከአደጋ ጥበቃ በማግኘት በኩል ከወንዶች እጅግ ያነሰ እንደሆነ ብዙ ጥናቶች የሳያሉ፡፡ የሴቶች መብትን ማክበርና በውስጣቸው ያለውን አቅም ማውጣት እንዲችሉ እኩል እድል ማግኘት የሚስፈልጋቸው የፆታ እኩልነት ለማምጣት ብቻ ሳይሆን ዓለም አቀፍ የልማት ግብን ለመምታት ይጠቅማል፡፡

በኢትዮጵያ ከጠቅላላ ህዝብ 80% በገጠሩ ክፍል የሚኖረው ሲሆን አብላጫውን የግብርና ጉልበት የሴቶች ቢሆንም ምንም አይነት እውቅና ስለማይሰጠው ግብአቶቹ እና የህብረተሰብ ተሳትፎ ሁሉ በአባት ወይም በባል ቁጥጥር ስር ይውላል፡፡ ከሦስት ሴቶች አንድዋ አካላዊ፤ስነልቦናዊና የወሲብ ጥቃት ይደርስባታል፤ 65% ሴቶች ግርዛት ያስተናግዳሉ፤ የመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤት ከገቡ ሴት ህፃናት ውስጥ ግማሹ ብቻ 5ኛ ክፍል መድረስ ይችላሉ፡፡ (Gender Equality and Women Empowerment /Ethiopia/USAID-2020).

ወደ ርዕሴ ስመጣ ከላይ ያሰቀመጥኩት እውነታ በሴቶች እለት ተእለት እንቅስቃሴ ላይ ትልቅ ተግዳሮት እንደሆነ ግልፅ ነው፡፡ ሆኖም ግን ይህን ከባድ ጫና ተቋቁመው እና እኩል እድል መጠቀም እንዲችሉና ወደ (Equty) እንዲመጡ ቢደረግ ከውንድም በላይ ውጤታማ መሆን እንደሚቻል ያሳዩ በርካታ ሴቶች አሉ፤ ይህም የይቻላል ስሜትን ይፈጥራል፡፡ በአሁኑ ሰዓት የፆታ እኩልነት እንዲመጣ በሰፊው እንቅስቃሴ እየተደረገ ቢሆንም ሴቶች ተወዳዳሪ ሆነው በከፍተኛ ባለሞያነት ፤በኢኮኖሚውና እና በፖሊቲካው ያላቸው ተሳትፎ ካላቸው ቁጥር ጋር ሲወዳደር እዚህ ግባ የሚባል አደለም፡፡ እዚህ ላይ ከላይ ያስቀመጥኩት ችግር እንዳለ ሆኖ ሴቶች በቤተሰብ ደረጃ ከልጅነታቸው ጀምሮ በተለይ በታዳጊነት እድሜያቸው በሰውነታቸው ፤በስሜታቸው እና በአስተሳሰባቸው ላይ ከፍተኛ ለውጥ ሲመጣ ከወላጅ ወይም ከአሳዳጊ ጋር በቅርበትና በግልፅነት ለውጦችን እንዴት መቀበል እንዳለባቸው ስለማይወያዩ እና ግንዛቤ ስለማይሰጣቸው በዚህ ከባድ የእድሜ ክልል ላይ ለሚገጥሟቸው ጉዳዮች ሁሉ ከነሱ ጋር ተመሳሳይ በሆነ የእድሜ ክልል ላይ እና የግንዛቤ መጠን ካሉ ጓዶቻቸው ጋር ብቻ በመወያየት ጊዚያዊ ስሜታቸውንና ፍላጎታቸውን የሚያረካ ውሳኔ በመወሰን ወደፊት ሊሆኑ ያለሙትን ግብ ሳያዩ በአጭር ሲቀጩ የምናያቸው ሴቶች በርካታ ናቸው፡፡ ታዲያ በዙርያቸው ያለው ማህበረሰብ ደግሞ የኛ ሚና ምን ነበር ብሎ ሳይሆን የሚጠይቀው የተለመደውን አባባል አይ የሴት ነግር በማለት ተስፋ አስቆራጭ የሆነ አስተያየት ከመስጠት ውጪ አስተማሪ የሆነ ግብዓት ሲሰጥ አይታይም፡፡

እኔ ግን አጥብቂ መከራከር የምፈልገው ምንም እንኳን ሴት በመሆንዋ ሊገጥማት የሚችትለው ነገር ብዙ ቢሆንም ከፊትዋ የሚገጥሟት መሰናክሎች መውጣት የምትችለው የራስዋ የሆነ ርእይ እና የህይወት ተልዕኮ ሲኖራት ነው፡፡ አንድ ሴት መሆን የምትፈልገውን ነገር ዛሬ ላይ ሆና ማየት (ማለም) ከቻለች በየዕለቱ የሚገጥምዋት ነገሮች ሁሉ ወደ ፈለገችው ቦታ ለማድረስ የሚያግዙ ናቸው ወይስ እንዳትደርስ የሚያሰናክሉ ናቸው እሚለውን መለየት ያስችላታል ፡፡ Sean Covey : The Seven Habit of Highly Effective Teen በሚለው መፅሃፊቸው እንዳስቀመጡት (Proactive People) በአመክንዮ መልስ የሚሰጡ ሰዎች እለት እለት በነሱ ላይ የሚፈጠር ነገር ሁሉ መቆጣጠር እንደማይቸሉ ተገንዝበው እያንዳንዱን ሁኔታ ወይም ተግዳሮት ምን አድርገው በቁጥጥር ስራ ማዋል እንዳለባቸው ያውቃሉ ይላሉ ፡፡ እኔም ፅሁፌን ሳገባድድ በሴትነታችን ሊገጥሙን የሚችሉ ነገሮች ብዙ ቢሆኑም ርእያችን እውን እንዳይሆን የማድረግ ጉልበት የምንሰጣቸው አልችልም በማለት የራስን አቅም ባለማወቅና ባለማሳድግ የምንፈጥረው የአስተሳሰብ ዉስንነት ዉጤት በመሆኑ ልንታገለዉና በአሸናፊነት ልንወጣዉ ግድ ይለናል፡፡

ነዋል አቡበከር
newalabubeker13@gmail.com

ምኞት ያሰከረው የሰው ልጅ የዘመን መለወጫ

ዘመን ከዘመን ሲለወጥ ፤ የዘመን መቁጠሪያዎችቻችን ወደፊት ሲራመዱ ፤ አዲስ አመት ሲጠባ ፤ አደይ ሲፈነዳ ፤ ምድርን ተስፋ ሲሞላት እኛም "እሰይ አዲስ አመት እንቁጣጣሽ እንኳን ደህና መጣሽልን" ብለን መቀበል፤ ከመፈቃቀሩም ከመጠያየቅ መዘያየሩንም ሁሉ ያውቅበታል ሀበሻ:: ታዲያ ከነዚህ ጋር ሁሉ አብሮ የሚሄደው ጥልቅ የመለካም ዕድል ምኞት መብዛት አስገረመኝና ለመሆኑ ሌላው አለምስ አዲስ አመትን እንዴት ያከብር ይሆን ስል የ Google ን ቋት በረበርኩኝ::ያገኘኂቸው መረጃዎች ግን አጃኢብ የሚያሰኙ ሆነው አገኘዋቸው:: ለካስ ባለፉት ነገሮች የተማረረው የሰው ልጅ በአዲሱ አመት መልካም እድል እንዲገጥመው የማያደርገው ድርጊት ፤ የማይከውነው ነገር የለም::

የምተርክላቹ በእንግዳ ባህልና ልምዳቸው አለምን ስለሚያስገርሙት የኬንያ አርብቶ አደሮች ወይም የሀመር ሰዎች አልያም የአማዞን የጫቃ ነዋሪዎች አይደለም:: የማወራቹ አጉል ልምድና ባህልን ፤ ምክንያት አልባ ድርጊትና እምነትን አልፈናል ስለሚሉትና ስለሚንቁት የምዕራባውያን ሀገራት አዲስ አመታቸውን መልካም ለማድረግ የሚከውኑት አሰገራሚ አንዳንዴም አስቂኝ ልምድ ነው::

ለምን ከአየር ላንድ አንጀምርም:: እንደው አንዳንድ ግዜ ህይወት ምርርር አድርጋቹ ፤ መኖር አንገሽግሿቹ "እረ የት ሂጄ ኡኡኡኡ ልበል?" ብላቹ አታውቁም? "እንደው መንግስት ግን ምን አለ የመረረው ሁሉ እየሄደ "ኡኡኡኡ" ብሎ ያለ ሀፍረት የሚተነፍሱበት ተቋም ቢያቋቁም::አሁን እንባን ከመጠበቅ ይሄ አይቀልም?" ብለው ተመኝተው አያውቁም? የኛ ይቆየን:: አየርላንዳውያን ግን ለዚህ ፍቱን መፍትሄ አዘጋጅተዋል:: በእነሱ የአዲስ አመት ወቅት የተለመደ አንድ ልምድ አለ:: ዳቦ ደጃፋቸው ላይ ማንጠልጠል::"መጥፎ መንፈስን አሽቀንጥሮ የበዛ ፀጋን ይስባል "ብለው ያምናሉ:: ታዲያ የዳቦው መጥፍ መንፈስን የማስወጣት ስራ የሚሰራው እስከ ደጃፍ ድረስ ብቻ ነው:: ከዚያ በኂላ ፍፁም እንዲጠፋ የሚከወን አንድ ድርጊት አለ:: ከቤት የወጣው ክፉ መንፈስ ፈቀቅ ብሎ ከደጃፍ እንዳይጠብቃቸው በእኩለ ለሊት ድቅድቅ ጨለማ ወደ በራፋቸው ይወጡና "ኡኡኡኡኡኡኡ" ብለው በጩኸት ያቀልጡታል:: ህፃን አዋቂው፤ አዛውንት ወጣቱ የሚችለውን ያህል ሁሉ ይጮሀል:: በጩኸቱ የድሮውን አባሮ "አዲስ አመት ሆይ በል አሁን ግባ" ሊሉ:: ደግሞ ይኼኛው አርጅቶ ጮኸው እንዳስገቡት ጮኸው እስኪያወጡት::

አስተውሉ እንግዲ አየርላንዳዊያን አዲስ ዘመንን አስታከው አገር ምድሩን በጩኸት ሲያቀልጡት የዴንማርክ ሰዎች ደግሞ አዲስ አመትና የቤት እቃ መስበር የኛ እንቁጣጣሽና አበባይሆሽ እንደማለት ነው:: አይነጣጠሉም::ልክ የኛ ታዳጊዎች አዲስ አመት ሲደርስ ስዕል ስለው አልያው ካርድ አዘጋጅተው ስጦታ እንደሚሰጡት ዴንማርካውያንም በአዲስ አመት የፍቅር መግለጫ ድርጊታቸው የቤት እቃዎቻቸውን አውጥተው የወዳጆቻቸው ቤት ላይ እንደ ናዳ መሰባበር ነው::ብርጭቆ አይቀር ሸክላ ፤ ማንኪያ አይቀር ሹኪያ ከማዕድ ቤት እየተጓዘ ሊያውም በእኩለ ለሊት ይወረወራል ይሰበራል:: "ታዲያ የሚወረወርበት ሰው ምንም አይልም?"ብለው ግራ እንዳዳይገባዎት:: የዴን ማርክ አባወራ የወዳጆቹን ብዛትና የፍቅራቸውን መጠን የሚለካው ከደጃፉ በተከመሩ የእቃ ስብርባሪዎች ነው:: ለሊቱ በብርጭቆ ስባሪ ካልተናወጠ ፤ጣሪያው ካልተንጋጋ አውዳመቱ አይደምቅም አይሞቅም::

መቼም በበዐል ወዳጅ ዘመድን መጠየቅ የበዐሉ ድምቀት መሆኑ ጥርጥር የለውም::"ተሰብስበው ካልበሉ፣ ካልተጓራረሱ፣ ካልተገባበዙ ምኑን በዐል ሆነ " ይሉ የለ ደጋግ እናቶቻችን:: ነገር ግን በዐሉ የሚከበረው ከሙታን ጋር ወይም ከእንሳስ ጋር ሲሆንስ? አዎ ቺሊያውያን የዘመን መለወጫን የሚያከብሩት ከሙታን ወገኖቻቸው ጓን እያወጉና እየተጨዋወቱ ነው:: ሮማንያን በበኩላቸው አዲስ አመት የቤት እንስሳዎቻቸውን ማዕድ ጋብዘው በቋንቋቸው ሊያወጓቸው እየጣሩ በአሉን በደስታ ያሳልፋሉ:: በበሬውን ወይም በጉን ፣፤ ዶሮውን አልያም ፈረሱን ከመዐዱ ጋብዘው "ብሉ በሞቴ... ያዙ እንጂ... ከምን ልጨምር" እየተባባሉ መሆኑ ነው:: ለምን ቢባል? መልካም እድልን ፍለጋ ነው:: ይህ ድርጊት መልካም ፀጋን እንደሚያመጣ ስለሚያምኑ::

የመልካም ነገር ናፍቆት ሪስያውያንም ብዙ ያደርጋል:: በሩስያ የአዲስ አመት ዋዜማ የሚከወን አንድ የታወቀ ልማድ አለ:: ታዲያ ችቦ ማንደድ አይደለም:: እንዲህ ነው ነገሩ:: የአዲስ አመት ዋዜማ ምሽት ላይ ሩሲያውያን በያሉበት ሆነው በቀጣዩ አመት እንዲሆንላቸው የሚፈልጉትን ነገር በወረቀት ይዘረዝራሉ:: ዘርዝረውም አያበቁም ያቃጥሉታል::

ማቃጠላቸውም አይደለም አስገራሚው ነገር:: አመዱን ሰብስቦ በማንሳት ከውስኪ ጋር ቀላቅለው ግጥም አድርገው መጠጣታቸው እንጂ:: ያለፈውን መጥፎ ትዝታ ፍቆ መጪውን ብሩህ ያደርገወ ዘንድ የሰው ልጆች የሁሉም ግዜ ተስፋ ነው:: አዲስ አመት ሲመጣ ደግሞ ይህ ስሜት ገዝፎ ልምድና ባህልን ወለደ:: ይህም ብዙ አስደናቂ እምነቶችን እንዲፈጥር አደረገው:: እናም ምኞት ያስከረው የሰው ልጆች የአዲስ አመት አከባበር እንዲህ ባሉ አጃኢበተኛ ድርጊቶች የታጀበ ሆኗል ነው የዚህ እትም የአጃኢብ አምዳችን ተረኩ:: ታዲያ እንደ ኢትዮጵያዊ ቀጣዩ አመት መልካም ይሆን ዘንድ እሪሪ ብሎ መጮህ ወይም እቃ መስበር አልያም አመድ በውስኪ መጨለጥ አያስፈልገንም::ከየፈጥሮ ጋር የተናበበ በውበትና ስነ ስርዐት ያማረ ውብና የሚያኮራ የመልካም ምኞት መግለጫ ባህል አለን:: ምርቃቱ ቄጤማው አበባውና ፀሎቱ ሁሉ! ይህን ጠብቆ ማቆየት ይገባናል:: አንባቢያን ሆይ አዲሱ አመት ከመመኘት ወደ ማግኘት የምንለወጥበት፤ እንደ አደይ ህልማችን የሚፈካበት፤ እንደሳሩ ተስፋችን የሚለመልምበት ፤እንደ መሬቱ አረሙ ከስሞ ፍሬው የሚያብብበት ይሁንልን:: ስደተኛው ለቤቱ ቤተኛውን ለክብር ያብቃልን:: ፍቅራችንን መከባበር ፤ መከባበራችን መተላለፍን ይውለድልን:: በቅንነታችን በበጓነታችን እና ለሀገር ወዳድነታችን የሚሆን ሰፊ ልቦና ያለምልምልን::

ሰናይ አዲስ ዘመን!

ያደውሉልን! 0912178520 0920019699

ዶ/ር እዮብ ማሞ

Don't get me WRONG again

እንደገና እንዳትሳሳቱ . . .

እንደ አዋቂዎቹ ግምት ከጥቃቅኖቹ አንስቶ ወሳኝ የሆኑትን ጨምሮ በየቀኑ ከሰላሳ አምስት ሺህ ያላነሱ ውሳኔዎችን አስበንና አሰላስለን እንወስናለን ይባላል፡፡ አስቡት! በ2013 ባሳለፍናቸው 365 ቀናት ውስጥ አናሳዎቹንና አንጋፋዎቹን ጨማምሮ በድምሩ ከ12 ሚልየን በላይ ውሳኔዎችን አድርገናል ማለት ነው (ለማመን ቢያስችግርም)፡፡

ቁጥሩ በዛም አነሰም የከትናንት ወዲያ ውሳኔያችንን ትናንት ኖረን አልፈናል፤ የትናንትናውን ውሳኔ ደግሞ ዛሬ እየኖርነው ነው፡፡ ስለሆነም የነገውን ኑሮ ለመቀየር ካስፈለገ የዛሬን ውሳኔ በሚገባ ማጤን አስፈላጊ ነው፡፡

አንዳንዶቻችን በ2013 ዓ/ም የወሰንናቸው ውሳኔዎች ውጤትም ሆነ መዘዝ አብሮን ወደ 2014 ይሻገራል፡፡ ያለፈው ስላለፈ፣ እንዲሁ ከመጸጸት ይልቅ መጪውን እንዴት እንደምናደርገው በሚገባ ማሰብ ይበጃል፡፡

ስሌቱ አጭርና ግልጽ ነው፡፡ የተዛባ ውሳኔ የተዛባ ሕይወት! ይህ ስሌት የእናንተን ሁኔታ የሚጠቁም ከሆነ ልክ አንደ 2013ቱ ይህ እንዳይሆን ከፈለጋችሁ ሶስት እርምጃዎች ያስፈልጓችኋል፡፡

1. ማንኛውንም ውሳኔ ከመወሰናችሁ በፊት ውሳኔያችሁ ከዋናው የሕይወት ዓላማና ከዋና ዋናዎቹ የሕይወት እሴቶቻችሁ ጋር መጣጣሙን እርግጠኞ ሁኑ፡፡

2. ማንኛውንም ውሳኔ ከመወሰናችሁ በፊት በሚገባ ለማሰብ በቂ ጊዜ መውሰዳችሁን እርግጠኞች ሁኑ፡፡

3. ማንኛውንም ውሳኔ ከመወሰናችሁ በፊት (በተለይም ጠንከር ያሉትን) በልምምድና በጥበብ ከእናንተ ቀደም ያሉ ሰዎችን አማክሩ፡፡

በ2013 ዓ/ም ደጋግማችሁ ያደረጋችኋቸውን ነገሮች መለስ ብላችሁ ብትመለከቱ በዚያው ዓመት ያዳበራችኋቸውን ልማዶች ያመለክቷችኋል፡፡ አንዴ የተደረገ ተግባር የመደገሙ እድል የሰፋ ነው፡፡ ስለዚህ አንድን ተገቢ ያልሆነ ተግባር ቀድሞውኑ አለመጀመር ይሻላል፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ የተደጋገመ ተግባር ወደ ልማድ የመቀየሩ እድል የጎላ ነው፡፡ ስለዚህ አንዴ ያደረግነው ነገር ጤና-ቢስ እንደሆነ እንዳሰብም ላለመድገም መጋደል የግድ ነው፡፡

አንድ ጊዜ ከጀመርነው በኋላ ብንደጋግመው ምንም ችግር እንደሌለበት አስበን የደጋገምነውና ወደ ልማድ የተቀየረው ነገር የሕይወትን አቅጣጫና ፍጻሜ የመለወጥ አቅም ይህ ነው አይባልም፡፡ ይህ የሚሆንበት ምክንያቱ የምናዳብራቸው ልማዶች ሕይወትን አስረው የማስቀረት ጉልበት ስላላቸው ነው፡፡

ሕይወታችሁ መታሰሩን ማወቅ ከፈለጋችሁ ቀላሉ መንገድ የሚከተሉትን ጠቋሚዎች ማየት ነው፡፡ ቀድሞ በጉጉት ታደረጓቸው የነበሩ መልካም ነገሮችን ካቆማችሁ፣ ውስጣችሁ ያለው አቅም ትልቅ፣ የምታከናውኑት ነገር ግን ትንሽ መሆኑን ካያችሁ፣ ከጊዜ ወደጊዜ ከማደግ ይልቅ እዚያው ከረገጣችሁ ወይም ወደኋላ ከቀራችሁ . . . በአጉል ልማድ ታስራችሁ ይሆናልና ሁኔታውን አጢኑት፡፡

ሶስት ጥያቄዎች ይመለሱ . . .

1. በ2013 ዓ/ም የጀመርኩትና በ2014 ዓ/ም የግድ ማቆም ያለብኝ አጉል ልማድ ምንድ ነው?

2. በ2014 ዓ/ም አጉል ልማድ ከማዳበር ይልቅ ጠቃሚ ልማዶችን ለማዳበር እንድችል ምን ምን አይነት የሕይወት ዘይቤ ለውጥ ማድረግ ይኖብኛል?

በ2013 ዓ/ም አብዛኛውን የሕይወታችሁ ሰላም የነሳችሁን ሁኔታ ብትመለከቱት ጉዳዩ ከሰዎች ጋር ተገናኝቶ እንደምታገኙት ምንም ጥርጥር የለኝም፡፡ ማታ ከማንቀላፋት ያስመሻችሁ ነገር፣ ሌሊት ቀስቅሶ እንደገና እንዳትተኙ ያደረጋችሁ ሁኔታ፣ ጠዋት ስትነቁ በመጀመሪያ ወደ ሃሳባችሁ የመጣው ሃሳብ፣ የቀን ሰላማችሁን የነሳው ነገር . . . አብዛኛው ከሰዎች ጋር የተገናኘ ነው ብዬ እንድገምት ይፈቀድልኝ፡፡

እውነታው ይህ ከሆነ፣ በ2014 ዓ/ም ልክ እንደ 2013ቱ እንዳትጨነቁና እንዳትጨናነቁ ከፈለጋችሁ ከሰዎች ጋር ያላችሁን ግንኙነት በከፍተኛ ማሕበራዊ ብልህነት የመያዝን ነገር ማዳበራችሁን አትዘንጉ፡፡ ያንን ለማድረግ ግን ያለፈውን የማራገፍን ስራና መስራትንና ለወደፊቱ ጥበብን የማዳበርን ስራ እንደሚጠይቅ አስታውሱ፡፡

ሶስቱ ወሳኝ ጥያቄዎች . . .

1. ወደ 2014 ዓ/ም ከመሻገሬ በፊት ይቅርታ መጠየቅ ያለብኝ ሰው ማን ነው?

አስታውሱ! ሰዎችን ይቅርታ መጠየቅ ማለት መሸነፍም ማሸነፍም ማለት አይደለም፤ በቀላሉ እውነታን መኖርና ሰው መሆን ማለት ነው፡፡ ሰዎችን ይቅርታ መጠየቅ ይህ ነው የማይባል ሰላምና ነጻነትን ይሰጣችኋልና ያጠፋችኋቸውን ሰዎች ይቅርታ በመጠየቅ ለራሳችሁ ትልቅ ቁም-ነገርን ስሩ፡፡

2. ወደ 2014 ዓ/ም ከመሻገሬ በፊት ይቅርታውን መቀበልና ያለፈውን መተው ያለብኝ ሰው ማን ነው?

አስታውሱ! ለሰዎች ይቅርታን መስጠት ማለት ይቅርታ ካደረግንላቸው በኋላ ልክ እንደ ቀድሞው መሆን ማለት ላይሆን ይችላል (የትዳር ግንኙነትን አይወክልም)፡፡ ለሰዎች ይቅርታን ካደረግን በኋላ ከሰዎቹ ጋር የሚኖረንን የወደፊት ግንኙነት እንደገና የማንጎዳበት አይነት ግንኙነት የማድረግ መብቱም ሆነ ሃላፊነቱ እንዳለን መዘንጋት የለብንም፡፡

3. በ2014 ዓ/ም አላስፈላጊ የሆኑ የሰው-ለሰው ግንኙነት ስህተቶችን የመቀነስን ጥበብ ማዳበር የምችለው እንዴት ነው? አስታውሱ! ማንኛውም የሰው-ለሰው ግንኙነት ቀላል አይደለም፡፡ የየቀን ሕይወታችሁን አብዛኛውን ጉልበት የሚወስደው የሰው-ለሰው ግንኙነት ጉዳይ ነው፡፡ ስለሆነም፣ በመጪው ዓመት ይህንን ክህሎት በማዳበር ጉዳይ ላይ ታላቅ ትኩረት እንድትሰጡ ትመከራላችሁ፡፡

የ2013 ዓ/ም ጉዟችሁ የተሳካለት ወይም የባከነ መሆኑንና አለመሆኑን ለማወቅ ከፈለጋችሁ ቀላሉ መንገድ ወደ ዓመቱ ከመግባታችሁ በፊት ያወጣችኋቸው ግቦች የመኖራቸውንና ያለመኖራቸውን ሁኔታ ማጤን ነው፡፡

ወደ 2013 ዓ/ም ምንም ግብ ሳይኖራችሁ ገብታችሁ ከነበረ የደረሳችሁበትንና ያገኛችሁትን ነገር ሁሉ እንደ “ግብ” እየቆጠራችሁ አንድም ነገር ከዓላማ አንጻር ሳታከናውኑ እድሜያችሁን እንዳባከናችሁ አትዘንጉ፡፡

በተመሳሳይ ሁኔታ ወደ 2013 ዓ/ም ግብ ይዛችሁ ተሻግራችሁ ሳለ ግቡን ሳትመቱ ዓመቱ እንዳለፈ ከተገነዘባችሁ አሁንም እድሜያችሁን እንዳባከናችሁ አስታውሱ፡፡

2014 ዓ/ም እንደገና እንዳይባክን ከፈለጋችሁ የሚከተሉትን ሶስት መመሪያዎች ተግባራዊ ማድረግ ትችላላችሁ . . .

1. ግባችሁን ግልጽ አድርጉ፡፡

ሕይወት አቅጣጫ እንዲይዝ ካስፈለገ የግድ ግብ ሊኖረው ይገባል፡፡ ግብ የሌለው ሰው አቅጣጫ የሌለው ሰው በመሆኑ ከየት እንደመጣ፣ የት እንዳለና ወደ የት እንደሚሄድ ለማወቅ ያስቸግረዋል፡፡ እግረ መንገዴን ግቦቻችሁ ከዋናዋ የሕይወት ዓላማችሁ አንጻር መቃኘት እንደሚገባቸው ላስታውሳችሁ፡፡

2. ግባችሁን የቀን ገደብ አብጁለት፡፡

ሕይወትን አቅጣጫ የሚያስይዘው ግብ የመሆኑን ያህል፣ ይህ አቅጣጫ ያስያዘን ግብ ስኬታማ የሚሆነው የቀን ገደብ ሲኖረው ብቻ ነው፡፡ የቀን ገደብ ያልወጣለት ግብ የመሬት ስበት በሌለበት ህዋ (Space) ወይም ጨረቃ (Moon) ላይ እንዳለ ቁስ ወዲህና ወዲያ ሲዋልል ይገኛል፡፡

3. በምንም ነገር ከግባችሁ ግራና ቀኝ አትበሉ፡፡

ሕይወት ግብ ሲኖራት አቅጣጫ ትይዛለች፣ ግብ ደግሞ የቀን ገደብ ሲበጅለት የስኬት መስመር ውስጥ ገባል፣ የቀን ገደብ የተበጀለት ግብ ደግሞ ወደ ግራና ወደቀኝ ሳንል ስንከተለው ብቻ የመሳካቱ ጉዳይ እውን ይሆናል፡፡

መልካም የአዲስ ዓመት ዋዜማ ለእናንተና ለቤተሰቦቻችሁ!!!
ምንጭ- ከዶ/ር እዮብ ማሞ የትስስር ገፅ የተወሰደ

ፍራኦል መስፍን
firaolmesfin8@gmail.com

የማይታይ ቁስል

የህይወት ገጠመኝ የሌለው ሰው ይኖር ይሆን ? ይብዛም ይነሰም ሁላችንም ዛሬ እስካለንበት ድረስ ለመልካም ነገር ወይም ደግሞ ለመጥፎ ነገር ተጋልጠናል፡፡ ብዙ ሰዎች እጅግ አስደንጋጭ ነገር በራሳቸው አልያም በቤተሰቦቻቸው ላይ ገጥሟቸው ተጨንቀው፣ ተረብሸው ኑሮን በመከራ ይኖራሉ፡፡ በአደጋ (ተሽከርካሪ)፣ በወንጀል (በድብደባ፣ ስለት መወጋት)፣ በጦርነት፣ ጾታዊ ትንኮሳ፣ ተፈጥሮዊ አደጋ (ጎርፍ፣ እሳት፣ መሬት መንቀጥቀጥ) ወዘተ በኋላ የሚፈጠር የአዕምሮ ህመም ድህረ ሰቀቀን ጭንቀት (Post-Traumatic Stress Disorder) በመባል ይታወቃል፡፡ ከአሰቃቂ ሁኔታ በኋላ የሚፈጠር ጭንቀት (ፒቲ ኤስ ዲ) በቀድሞዎቹ ዓመታት የሚታወቀው ሼል ሾክ (የጦር ሜዳ ጭንቀት) በሚል ስያሜ ሲሆን ስለ በሽታው ይደረጉ የነበሩት ጥናቶች በዋነኛነት ያተኩሩ የነበረው ከዘመቻ በተመለሱ ወታደሮች ላይ ነበር፡፡ ዛሬ ብዙ ነገሮች ተለውጠዋል፡፡ ወታደር ባትሆንም እንኳ ፒ ቲ ኤስ ዲ ሊያጋጥምህ ይችላል፡፡ የሆነ ዓይነት አሰቃቂ ሁኔታ ከደረሰብህ ለእንዲህ ዓይነቱ ጭንቀት ልትጋለጥ ትችላለህ፡፡ ሁኔታው የጦር ሜዳ ውሎ ወይም የግዳጅ ወሲብ ለመፈጸም የሚደረግ ሙከራ አለበለዚያም የመኪና አደጋ ሊሆን ይችላል፡፡ ብቻ ይህ ሁኔታ ከተፈፀመብን ፣ ወይም ሲፈፀም በስፍራው ከነበርን አልያም ከሰማን የዚህ ጭንቀት ሰለባ የመሆን እድላችን ሰፊ ነዉ ፡፡

ሆኖም ሁሉም አሰቃቂ ሁኔታዎችን ያሳለፈ ሰዉ ሁሉ ከአሰቃቂ ሁኔታ በኋላ የሚፈጠር ጭንቀት (PTSD) ያጋጥመዋል ማለት አይደለም፡፡ ነገር ግን በርካታ አሰቃቂ ሁኔታዎች ሲፈራረቁ ሰዎችን ይበልጥ አደጋ ላይ እንደሚጥሉ እናውቃለን፡፡ ድንገተኛ የሆነ አስደንጋጭ ሁኔታ በሚያጋጥምበት ጊዜ ሰውነት አንዳንድ ሆርሞኖችን በከፍተኛ መጠን በማመንጨት እነዚህ ሆርሞኖች የስሜት ሕዋሳት ለአደጋ በተጠንቀቅ እንዲቆሙ ያደርጋል፡፡ እንደ ወትሮው ቢሆን የሆርሞኖቹ መጠን አደጋው ካለፈ በኋላ ወደ ቀድሞ መጠናቸው ይመለሳሉ፡፡ በፒ ቲ ኤስ ዲ ሕሙማን ላይ ግን ከፍ እንዳሉ ይቆያሉ፡፡

አሰቃቂ ሁኔታ አጋጥሞህ ከነበረና ሁኔታው ተመሳሳይ ችግር ጥሎብህ የሄደ ከሆነ ይህ የደረሰው ባንተ ላይ ብቻ አለመሆኑን መገንዘብህ በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ ፒ ቲ ኤስ ዲ ማንም ሰው ሊያጋጥመው የሚችል ቀውስ ነው፡፡ ከስርጭት አንፃር PTSD ሴቶች ለይ ይበዛል፡፡ 10 በመቶ ለሴቶች (ጾታዊ ጥቃት ስለሚበዛ) ፣ 4 በመቶ ለወዶች (ከግጭት ጋር በተያያዘ) እንዲሁም ወታደሮች ለይ 30 በመቶ እንደሚጠጋ ጥናቶች ያሳያሉ፡፡ ወጣቶች ላይ ደግሞ ስርጭቱ እጅግ ከፍተኛ ነው፡፡

ማንም ሰው ከዚህ ችግር የተጠበቀ አይደለም፡፡ ነገር ግን ማህበራዊ ተሳትፏቸው አነስተኛ የሆኑ ሰዎች የበለጠ ሊጠቁ ይችላሉ፤ እንደ ምሳሌ ብቸኛ ሰዎች፣ ትዳር የሌላቸው(በሞት አልያም በፍች ሊሆን ይችላል) ፣ ከፍተኛ ድህነት ዉስጥ ያሉ (የወንጀል ሰለባ ሰለሚሆኑ)፣ አብዝቶ የሱስ ተጠቃሚዎች፣ አንዳንድ የስብእና ችግር አይነቶች፣ ተያያዥ ጭንቀቶች እንዲሁም ድባቴ በጥቂቱ የሚጠቀሱ ናቸው፡፡

ምልክቶቹ

1- ለአሰቃቂ ነገር ተጋላጭ ከሆኑ በኋላ የሚፈጠር ነው።
በራሳቸው ላይ የተፈጠረ ገጠመኝ ሲሆን፣ ሌሎች ሰዎች ላይ ሲደርስ መታዘብ፣ በቤተሰብ አባል ላይ መድረሱን ሲያዉቁ፣ እና ተደጋጋሚ አጋላጮች ሲኖሩ (የአደጋ ጊዜ ሰራተኞች)
2- ተመላላሽ፣ ጣልቃ ገብ የሆነ የሚረብሽ ትውስታ፣ ቅዠት፣ ሰመመን ዉስጥ መግባት።
አደጋው እንደ አዲስ በእዉን የሚፈጠር ይመስላቸዋል፣ ሁኔታዉን እንደነበረው ይተገብሩታል፣ ፍንጭ የሚሰጡ ነገሮች (ሲሰሙ፣ ሲያዩ) ይረብሻቸዋል።
3- የጸና ሽሽት ውስጥ ይገባሉ።
ስለሁኔታው ትዉስታ የሚሰጣቸውን ላለመስማት፣ ላለማየት፣ ሰዎችንም ላለማግኘት በጽናት ይሸሻሉ። ትውስታውንም ለመርሳት ሱስ ይጠቀማሉ።
4- አሉታዊ አስተሳሰብ እና ስሜት ይኖራቸዋል
"እኔ መጥፎ ነኝ፣ ማንም ሰው አይታመንም፣ አለም ክፉ ናት" የሚሉ አስተሳሰቦች በግለሰቡ ላይ ይነግሳሉ። እራስን መውቀስ ራስን ለማጥፋት ሲገፋፋ፣ ሌሎችን መውቀስ ደግሞ ለከፋ የአዕምሮ ጤና መታወክ፣ ሱሰኝነት ብሎም ክፋት ይዳርጋል። ፍርሃት፣ ቁጭት፣ ቁጣ መገለጫቸው ይሆናል። ስሜቶች ቁጥጥር ከሌለው ሌሎች ሰዎችን ሳያውቁት ሊጎዱ ይችላሉ።
5- ድንጉጥ እና ደንታ ቢስ ሊሆኑ ይችላሉ።
ቶሎ ይቆጣሉ፣ ሁሉንም ነገር በነቂስ ይከታተላሉ፣ ይበረግጋሉ፣ ይወራጫሉም። እንቅልፍ ላይ ይሰቃያሉ፣ በህይወታቸውም ደንታ ቢስ ይሆናሉ።
ህክምናው የስነልቦና እንዲሁም የመድሃኒት ናቸው። ጊዜ የሚፈልግ እና ቀስ በቀስ በሂደት የሚስተካከል የህመም አይነት ስለሆነ በጊዜ ከታከመ ዉጤታማነቱ አመርቂ ይሆናል።
ቸር እንሰንብት
ምንጭ (DSM 5)

ጉቺ ሽመልስ

የቴዲ አፍሮና የጂጂ ኢትዮጵያና አደዋ በወፍ በረር

((ይህ ፅሁፍ ጭብጣዊ ቅኝት እንጂ ማወዳደር የማይዳዳዉ አጭር ዳሰሳ ነዉ::))

ጥበባዊ ስራዎች ባላቸዉ ዋጋ ከመዳኘት ይልቅ ቲፎዞአዊ ዝንባሌ ባላቸዉ ተደራሲያን ዋልታ ረገጥ ቡራኬ እና እርግማን ማስተናገድ እጣ ፈንታቸዉ ሆኗል:: የማወዳደር ልክፍት ተጣብቶናል::

'ከአዳም ረታ እና አለማየሁ ገላጋይ?'
'ከኤፍሬም ስዩምና በዕዉቀቱ ስዩም ማን ይበልጣል?'
'ጂጂ ወይስ ቴዲ?'
ማብቂያ የለዉም::

ዘመነኛ ስራዎች በሂሳዊ ትንታኔ የመታየት እድል ተነፍገዋል:: ከያንያን ባበጁት ግላዊ ፍኖት የሚጓዙ እንደመሆኑ መጠን በራስ አራዳድና ምናብ ጉዳዩን ሊገልፁ ይችላሉ:: በዚህ ሁኔታ ማበላለጥ ጨርሶ የማይታሰብ ነገር ይሆናል:: በእርግጥ ስራዉ በሚኖረዉ ፍሬ ነገር እና በአድማጩ ግላዊ ብያኔ በር መጠርቀም የማይቻል በመሆኑ ሁሉም በጣዕም ልኬቱ አንዱን ማስበለጥ ተፈቅዶለታል:: በእኔ በኩል ግን   ታካች ንትርክን ለመክላት ቢበጅ በሚል ይህ ንፃሬአዊ አተያይ እዉን ሆነ::
እነሆ...

ፈር መያዣ

ሀገር ንድፉ ልቦና ላይ ነው:: ''ሀገር ሰው ነው'' የለም ''ጋራው ሸንተረሩ ወንዙ ነው'' አይነት ጉንጭ አልፋ ክርክር ውስጥ አንገባም:: አይሁዶች ለ1900 ዓመት ሀገር አልነበራቸው:: አርታርቲካ እና ሌሎች ሰው አልቦ በመሆናቸው ሀገር አይባሉም:: ባለቅኔው አያሙሌስ ፦

''የጤናዬን ነገር አደራ
የዘፍጥረቴንም ጭምር
ብቻዬን ትዬ አልቆምም
ያለ ፅንፈ አለሙ ድምር'' አዩደል የሚለው?

የቴዲ አፍሮ ኢትዮጲያ

የቴዲ አፍሮ የሙዚቃ ግጥሞች ወኔአምና ደም አሙቅ ናቸዉ::

"የሰለሞን ዕፅ ነሽ የቁድሳን ዕንባ ያበቀለሽ ቅጠል
ዛሬ አዲስ አይደለም በለኮሰዉ እሳት የነካሽ ሲቃጠል"

እነዚህ ስንኞች የኢትዮጵያን ጥንታዊነትና የህዝቦቿን አልበገር ባይነት ይገልፃሉ::
ድምፃዊዉ "ፍቅር ያሸንፋል" ባይ ቢሆንም የአንድ አፍቃሪ ታሪክ የሚተርከዉ"70"ደረጃ ሙዚቃዉ እንኳን ሳይቀር መውዜሩን አስቀምጦ ክራር ያነሳ ገፀባህሪ ነዉ:: በቅርብ ለጆሮ ባበቃዉ ሙዚቃዉም

"እንኳን ለጎረቤት ከወንዜ ለጠጣ
ቋያ እሳት ነዉ ክንዴ ከሩቅም ለመጣ"

አይነት ጀብዳዊ መልዕክት እናገኛለን::
ቴዲ ማህበራዊ እንግልታችንን ይሰቅቀዋል::

"አፈር ይዞ ዉስጡ አረንጓዴ
ለምን ይሆን የራበዉ ሆዴ?"

ሲልም አንጡራ ሀብት እያለን ከድህነት አረንቋ እንዳልወጣን በቁጭት ይጠይቃል::

"ብራናዉ ይነበብ ተዘርግቶ ባትሮንሱ ላይ
የነፋሲለደስ የነተዋናይ"

እያለ የስልጣኔ በኩር የነበርን ፣ የእድገት ማማ ላይ እንደነበርን ያወሳል::

"አንተ አበርሃም የኦሪት ስባት የእነ እስማኤል የይሳቅ አባት
ልክ እንደክሱም ራስ ቀርፀሃት ራሴን በፍቅር ጣፍ ለኩሳት ነፍሴን"

ተማፅንኦዉ የሰዉ ልጅ ሁሉ ሊኖረዉ የሚገባን አማናዊ ፍቅር የሻተ ነዉ::

የቴዲ ምናብ ለትላልቅ የታሪክ ድሎች ይሰግራል:: አሸናፊነት የሚመስጠዉም ይመስላል:: የነገር ሀቲቱንም የሚያዘግነዉ እንደ መቅደላ ፣ አደዋ ካሉ ቦታዎችና እንደ አፄ ቴዎድሮስ፣ አፄ ሚኒሊክና አፄ ሀይለ ስላሴ ካሉ ሰብኦች ነው:: ቴዲ በታሪካ የሚመሰጥ ይመስላል:: አፍቃሬ አፄዎች ነው ብንል እሳሳት ይሆን?

የቴዲ አደዋ

በአመዛኙ የዉትድርና ዉሎአቸዉን የሚተርከዉ ይሄ ሙዚቃ
"ባልቻ አባቱ ነፈሰ
መድፉን ጣለዉ ተኩሶ"
መሰል ምስል ከሳችና ታሪክ ነጋሪ ስንኞች ያሉበት ሲሆን ግጥማዊ ጨመቁን ስንመለከት ውጊያዉን ተራኪ እና በድሉ ተማራኪ ሆኖ እናገኘዋለን::

ጀጀባdha ኢጆሌ ቢየኮ
ዲናፍ ኢላዩ ኢትዮጵያ "

ሲሊም የኦሮሞ ፈረሰኞችን ገድል ያወሳል:: በዋሽንግተን ዊኒቨርስሲቲ የአፍሪካ ጥናት ተመራማሪው ፕሮፌሰር ሬይሞንድ ጆናስ ከጦርነቱ ሸሽተው የተመለሱ የጣሊያን ተዋጊዎችን ጠይቆ እንዳሳፈረው 'ፈረሰኞቹ እንደ "ጥቁር ደራሽ ወንዝ ነበሩ" ይላል::

ወይ ሳልለዉ ብቀር ያኔ
እኔ አልሆንም እኔ "

እያለም ለሚኒልክ የክተት አዋጅ አወንታዊ ምላሽ ለድሉ ጉልህ አበርክቶ እንዳለዉ ይመሰክራል:: እኔ እኔ የሆንኩት "የናኔዉ እኔ"(አባቴ) ወይ በማለቱ ነዉ አይነት ዉስጠ ወይራነትም አያጣዉም::

በአጠቃላይ የቴዲ ኢትዮጵያ ስነልቦና ካልነኳት የማትነካና ከተነካች ደግሞ የክተት አዋጅ አውጃ ህዝቦቿን ከዳር እስከ ዳር የምታሰልፍና ድልን የምትቀዳጅ ናት:: ቴዲ "በሼመደፈር" አንድነትን በልህቀት የሰበከ እንደ "አልሞላም ኪሴን" ያሉቱ ደግሞ ስራዎቹ የትዉልዱን ሞራል ለማነፅ የሚታትሩ ሆነዉ እናገኛቸዋለን::

#የጂጂ ኢትዮጵያ

ለእንስት እምብዛም ቦታ ና ክፍል በሌለዉ የሙዚቃ እንደስትሪና ለእንዲህ ላሉት ጉዳዮች ባድነት ለሚያጠቃዉ እንዲሁም ልማዱ ካልዳበረ ማህበረሰብ ወጥቶ ሙዚቀኛ መሆን አዳጋችነቱ ሊካድ የሚችል አይደለም:: ጂጂ በ ነዛሪ ግጥሞቿ እና ጆሮ ገብ ዜማዎቿ በርካታ ጭብጦችን ዳስሳለች:: የጂጂ ኢትዮጵያ የሶስት ሺ አመት እመቤት ናት::

"እቴ አንቺ የእኔ ሙሽራ እስቲ ልጠይቅሽ
ያገቡሻል ይፈቱሻል አሁንም ድንግል ነሽ"

ምን ያለ ድንግልና በመገባት በመፈታት የማይገሰስ? እመቤትነትና ሙሽራነትስ እንደምን ሰመሩ? የኢትዮጵያን ረቂቅነት በቅጡ የተረዱ ዉብ ስንኞች! ለጂጂ ኢትዮጵያ "የማንነት መለኪያ፣ ኩራትና ክብር" ናት::

#የጂጂ አደዋ

"የሰዉ ልጅ ክቡር ሰዉ መሆን ክቡር" በሚል የስንኝ መባቻ የሚጀምረዉ ይሄ ሙዚቃ የሰዉን ቦታ በተገባ ያብራራ ነዉ::

" ሰዉ ሞቷል ሰዉ ሊያድን ሰዉን ሊያከብር
በደግነት በፍቅር በክብር ተጠርቶ ..."

በጂጂ አደዋ ሰዉ ሊያድን ሰዉ ሞቷል:: ደግነት ክብር ና ፍቅር አስገድደዉት ነፍሱን ያለ ስስት በመስጠት የሞት ሲሳይ ሆኗል:: አጠቃላይ የሰዉ ልጆችን ታሪክ እስከወዲያኛዉ በተለይ ቀለም ተኮር ንቀትን የሻረዉ የአድዋ ድል በጂጂ ብዕር ሲገለፅ መሪረ መስዋዕትነቱ የእልፎችን አጥንት ከፍሎ የደም ሀይቅ ሰርቶ የመጣ እንጂ የዋዛ ድል እንዳይደለ በምናብ አድዋ ድረስ በመዉሰድ ያሳየናል:: የጂጂ አደዋ ህማሙ አልቀረዉም:: የተከፈለዉ ሰዉ እንደሆነ ላቅ ባለ ግጥማዊ አቅም ይቀርባል::

"የተሰጠኝ ህይወት ዛሬ በነፃነት
ሰዉ ተከፍሎበታል ከደምና ካጥንት"

በማለት የተከፈለዉን መሪሪ መስዋዕትነት ታነሳለች:: " አድዋ ዛሬ እናት አድዋ ትላንት መቼ ተነሱና የወዳደቁት"ም ስትል የመስዋዕትነቱን ዘመን አይሽሬነትና ለትዉልዱ ቀና ማለት የወደቁ እንዳሉ እንዳይዘነጋ ታሳስባለች:: የጂጂ አድዋ ምስክር ነዉ:: የጀግኖች አባቶቻችን ተጋድሎ ምስክር:: የጦር አዉድማዉ ነፍስ ግብር እማኝ:: ሌሎቹ ፍፁም ኢትዮጵያዊ የሆኑ ዜማዎቿም አይጠገቡም::

‘ማደሪያ የሌለዉ ግንድ ይዞ የሚዞረዉ’ዓባይ’ ለጂጂ “የማያረጅ ዉበት፣ የማያልቅ ቁንጅና”ነዉ።
አገዉኛ ዜማዋ እንኳ ሳይቀር ቋንቋዉን የማይናገሩትን የመማረክ አማላይነት አለዉ።

“ አንተ ሀገርህ ወዲያ (x2)
ከወንዙ ባሻገር
የእኔ ሀገር ከወዲህ ወንዙን ሳንሻገር
ታዲያ ምን አለበት ያም ሀገር ያም ሀገር
እስቲ ስምትልህ ስቀበር
አንተ ልጅ ዛሬን ከእኔ እደር”

የፍቅር ረሀብተኛዋ የተዋበች ሳዱላ በሞቴ አትሂድ ትለዋለች። ‘አገራችን’ እስከሆን ድረስ ያም ‘ሀገር ‘ያም ‘ሀገር’(ያም የእኔ ነዉ ይሄም ያንተ ነዉ) ትለዋለች።
በ”እኔን የራበኝ ፍቅር ነዉ”
“

ጎጃም ያረሰዉን ለጎንደር ካልሸጠ
ጎንደር ያረሰዉን ለጎጃም ካልሸጠ
የሸዋ አባት ልጅ ለትግሬ ካልሰጠ
እህህህ..”

እዚህ ጋ የገጣሚ ደበበ ሰይፉን “ከአክሱም ጫፍ አቁማዳ” እንድናስታውስ እንገዳደለን።
“ትግራይ ላከ ወሎ ጋ አበድረኝ ብሎ አንድ ቁና ጤፍ ወሎም አፈረና የለኝም ማለት..... ላከ ወደሸዋ “ ሸዋ ወደ ሀረር፣ ሀረርም ወደ ባሌ
እንዲህ እንዲህ እያለ ኢትዮጵያን አዳርሶ አቁማዳው አክሱም ጫፍ ላይ ይሰቀላል።
ደበበ እንዲህ ይላል፡-

“እኔና ወንድሜ ሁላችን ሁላችን
ከባዶ አቁማዳ ነው የሚዛቅ ፍቅራችን”

እኛ ኢትዮጵያዊያን እጦት ተጋሪ ገመናና ሸሻጊ ነን።

ጂጂ መግነጢሳዊ በሆነዉ መረዋ ድምፅዋ ከብዙዎች ልብ የቀሩ ስራዎችን አበርክታለች።
እኔን የራበኝ እንጀራ እህሉ፣ ወተቱ ወይ ጠጁ መስሏቸው ችግሬ ጭንቀቴ ምንጩ ያልገባቸው ያቺ ሰው ተራበች ሲሉ ሰማኃቸው” ስትልም ራህቧ ፍቅር መሆኑን ታፀናለች።

#እንደ መደምደሚያ
ሁለቱም በየፊናቸዉ ኢትዮጵያን እና ኢትዮጵያዊነትን በስራቸዉ ከማግዘፍም ባለፈ ከመለኮታዉ ጣልቃ ገብነትና ንትረክ ያልተላቀቀዉን ታሪካችንን በየራሳቸዉ ቀለም በቃላት ብሩሽነት በልባችን ፅላት ላይ ስለዋል/ቀርፀዋል።
ከበላይ ያለዉ የአጭር አጭር ዳሰሳ የሁለቱንም ከያኒያን አጠቃላይ ስራዎች ያልቀነበበ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ በተጠቀሱት ግጥሞች ላይ ተጨማሪ ሀሳቦችን ለማከል ለሚሻ ሙሉ ፈቃድ የሰጠ ነዉ።

ሀገራችን ልታድግ የምትችለው ሌሊቷ ቀን ሲሆንላት ብቻ ነው!

የምሽቱ ፀጥታም ይገርመኛል:: ይሄ ሁሉ ሕዝብ የዚችን ፀሐይ አወራረድ ሳያይ በየቤቱ ሲገባ ቅር አይለውምን? እላለሁ:: በየቤታቸውስ ምን ይሰራሉ? እላለሁ:: የሚሰሩትን አስቤ ከጥቂት ነገሮች የበለጠ መዘርዝር አልችልም" ይላል የግራጫ ቃጭሎቹ ተወዳጁ መዝገቡ ዱባለ::

ትዝ ሲለኝ ሌሊት 'ዎክ' የማድረግ ልምድ አላዳበርኩም:: የሌሊቱን ቁር ቀምሼም አላውቅም:: ታድያ ለምን ወጥቼ አላየውም? የሚል ሀሳብ ሰቅዞ ሲይዘኝ ስምንት ሰዓት ሊሆን ሲል ከቤት ወጣሁ:: የግቢያችንን መዝጊያ እንደከፈትኩ የመንገዱ መብራት ዐይኔን አጥበረበረኝ (በዚህ ሰዓት መብራቱን የሚጠቀመው ሳይኖር ለምን በራ? ቀን ከሚያጠፉብን ሰው የማይጠቀምበትን ሰዓት አውቀው አጥፍተው ኃይል ቢቀንሱስ? የሚል ሀሳብ በዐይኔ በኩል ገባ መሰል):: ዐይኖቼን አሻሽቼ ከዳጃችን ጀምሮ ቁልቁል የተዘረጋውን ኮብል ስቶን ተመለከትኩ፣ ተኝቷል:: ዛፎቹም እስኪነጋ ድረስ አልቦ እንቅስቃሴ ሆነዋል::

ኮብሉን ይዤ ወደዋናው አስፓልት አዘገምኩ:: ከርቀት አንድ መኪና እያጓራ ወደ'ኔ አቅጣጫ ይመጣል:: መኪናው በቀረበኝ ቁጥር ISUZU መሆኑንና ጫት ወደሌላ ከተማ እያደረሰ እንደሆነ ከልምዴ አወቅሁ:: ተገረምኩ:: አስፓልቱ ላይ ያለፈው አንድ መኪና ብቻ ነው:: ይሄ ማለት አንድ ገጠር ውስጥ ምናልባት በቀን ሊታይ የሚል መኪና ነው:: በዚህ ሌሊት በቋሚነት ሥራችን ብለው የሚሰሩት አካላት ትራንስፖርት አገልግሎት ከሚሰጡ አካላት ጋር ጥበቃ የሚሰሩ ሰራተኞች ናቸው (ፖሊስ፣ ዘበኛ):: (የሌሊቱን ጊዜ ተጨማሪ ክፍያ እየተከፈላቸው የሚሰሩትን ልብ ይሏል)::

ኢትዮጵያ ውስጥ መምሸት ማለት ለአብዛኛው ሰው ከሥራ መፋታት ማለት ነው ለካ:: በቀን ውሏችን ሳንሰራ የምናሳልፈው ጊዜ ለካ ሌሊታችንን እያራዘምንበት ነው? ለአስራ ስድስት ሰዓት ከሥራ ተፋትተን (ስምንቱንም ሳንሰራበት ቦጫጭቀነው) እንዴት እናድጋለን ብለን እናስባለን? እንቅልፍ እንቢ ሲል እንኳን ወጥተን የምንሰራበት፣ በሰዓት ጥቂት ክፍያ የሚከፍል ፋብሪካ ለምሳሌ የዱቄት፣ የካልሲ፣ የመሳሰሉት ነገሮች ቢኖር ብዬ ተመኘሁ:: ግን ሳስተውለው እኛ ኢትዮጵያውያን አንደኛ ሀገራችን ውስጥ ሲሆን ሥራ ትልቅ እና ትንሽ ብለን እንፈርጃለን፣ የክብር ጉዳይ (ውጪ እኮ ቢሆን ዝቅተኛውን እንደምንሰራ ይታወቃል) ሁለተኛ ሌላው የሰራው ሥራ አይጥመንም:: ከልብስ፣ ጫማ አቅም ጀምሮ እስከትናንሽ ምርቶች ድረስ 'ብራንድ' የምናማርጥ፤ ከሀገር ውስጡ ይልቅ የውጪው የሚያነሆልለን ነን:: ታድያ እኛ ያልተጠቀምነውን ማን ይጠቀመዋል? እኛስ ካልተጠቀምነው እንዴት እየተሻሻለ የሚሄድ ጥራት ያለው ምርት ይኖረናል? ታድያ እንዴት ይታደግ ይሆን? ገጠሮቻችን 'ቀን' የሚወጣላቸው ቀን መቼ ይሆን? የአንድ መኪና ድምጽ ከመስማት የሚያድጉበት... መብራት፣ ንፁህ ውኃ እና የመሳሰሉት መሠረታዊ ነገሮች የሚሟላላቸው መቼ ይሆን?

ሌላው በሌሊት ተጠቃሚ ሊሆን የሚችለው እድለኛ ሰው የኪነጥበብ ሰው ነው:: ምክንያቱም ሌሊት በራሱ ዉበት ነዋ! ቀን ሲሆን ከፀሐይ ጋር ብቻውን የሚያሳልፈው ሰማይ አኩኩሉ የሚጫወቱትን ጨረቃ እና ደመና.. የእነሱን ድብብቆሽ በታዛቢነት የሚመለከቱ እልፍ ከዋክብትን ስለሚያገኝ ብቸኝነቱን ይረሳል:: ወደቤቴ ስመለስ ሰፈሩ ጭር ማለቱ አስደሰተኝ:: ደራሲዎች ይህን ዝምታ እንዴት ይወዱት ይሆን? ቀን ቢሆን እኮ የህፃናቱ ቡረቃ፣ የድምጽ ብክለቱ፣ የአዋቂዎች ትርምስ ሰፈሩን የብድ ቤት ያስመስለው ነበር:: 'ከኳኳታው ተነጥለን- ዝም ብለን አብረን ዝም ለማለት' እንደሎሬት ጸጋዬ ገብረመድኅን ቆቃ ድረስ መውረድ አያስፈልግም:: ሌሊት በራሱ ቆቃ ነው:: መምሽቱን ደራሲዎች፣ ጥበቃዎች፣ ሾፌሮች እና ሌሎች በሌሊት የሚሰሩት የሚጠቀሙበት ከሆነ ሌላው ማኅበረሰብስ ምን ይሰራበት ይሆን? የግራጫ ቃጭሎቹ መዝገቡ ዱባለ እንዲህ ይለናል::

የሚሰሩትን አስቤ ከጥቂት ነገሮች የበለጠ መዘርዝር አልቻልኩም:: ይሔ ሁሉ ሕዝብ እነዚህን ትንሽ ትንሽ የመሰሉ ነገሮችን ይሠራል.....

ራት ይበላሉ (ካልበሉ ስለሚራቡ)
ይጠጣሉ (ካልጠጡ ስለሚደርቁ)
ይጫወታሉ (ካልተጫወቱ ስለሚያብዱ)
ይተኛሉ (ካልተኙ ስለሚደክማቸው)
ያወራሉ(?)

ውድ አንባቢ ሆይ ሌሊትህን በምን እያሳለፍህ ይሆን? ለሞት ታናሽ ወንድም እንቅልፍ እየተሸነፍክ? ወይስ ማንነትህን እየገነባህ? ራስህን ተመልከት....

#አልፍ ገጾች



የናስ ኀ/ማርቆስ
e-mail- lijyoha2@gmail.com

አስታውሳለሁ የግቢያችን በር ላይ በቀለም ምልክት የተደረገብን ቀን የሆንነውን መሆን:: ሰፈራችን ሁለት ሳይሆን ሁለት የሆነበትን ያንን ክፉ አጋጣሚ:: የተመደቡብን የሞት መላእክት የሚፈርስና የማይፈርስ፣ የሚቃጠልና የማይቃጠለውን ቤት በቀይ ቀለም ለይተው ካለፉ በኂላ ስንታመስ ዋልን:: ሐረር ለሲያል ቀረበች::ሞት የጠበቁት ቀን ቢመጣ ጥሩ ነበር ... አልሆነም:: ያለ እንቅልፍ ያለፈው ሌሊት ሌላ ብርሃን የለሽ ቀን ተክቶልን ሄደ:: አብዛኛዎቻችን ትርፍ የሌለው ደረቅ ምጥ አማጥን:: ቁርጠቱ ብርቱ፣ ሕመሙም ጽኑ ነበር:: በሰዓታት ልዩነት ውስጥ ነፍሳችን ከሳች፣ ቆዳችን ጠቆረ፣ ተስፋ የምናደርገው ነገር ሁሉ ከውስጣችን ሙጥጥ ብሎ አለቀ:: ከተፈጠርሁ ጀምሮ አስቤው፣ ሊኖር ይችላል ብዬም ጠርጥሬ የማላውቀውን ፍርሐት አካል ለብሶ ያየሁት ያን ቀን ነበር:: የነገሩ አካሄድ እየታያቸው ሐዘናችንን የተካፈሉ "አትፍሩ! ለበላይ አካል ጉዳዩን አሳውቀናል!" እያሉ ያጽናኑን ጎረቤቶች ነበሩ:: በዛው ልክ ደግሞ የእነርሱ ደጅ ስላልተንኳኳ ብቻ እንዳላየ፣ እንዳልሰማ ሆነው በዝምታ ያለፉም አልታጡም:: እንጥፍጣፊ ርሕራሄ ማሳየት አቅቷቸው ... መጥፋታችንን ለማየት የቸኮሉም ነበሩበት::አልቀረልንም ... የሚቀጥለው ቀን ከሌሊቱ ዘጠኝ ሠዓት ገደማ ከአንድ ጎጆ የድረሱልኝ ድምጽ ተሰማ:: አገር ምድሩ ሁሉ እኩል ኡኡታውን ያቀለጠው ያህል ከኀሊናዬ የማይጠፋ ጩኸት ሰፈሩን ደበላለቀው:: እኔና ፋሲል ኩርምት ብለን ከተቀመጥንበት በድንጋጤ ተነስተን ሮጥን:: ዞር ብሎ ማየት የሚታሰብ ነገር አልነበረም::ጀርባዬ እስኪበሰብስ፣ ግንባሬ በላብ እስኪታጠብ ወዴት እየሄድን እንደሆነ ያልየለት ሩጫችን እልባት ያገኘው ባጋጠመኝ እንቅፋት ምክንያት ነበር:: ውልክፍክፍ ብዬ ተደፋሁ:: ቀድሞውኑ ልቤ በፍርሐት ስለተሸረሸረ መትረፌን ማመን አልቀለለኝም:: እንደሌለሁ እየተሰማኝ መኖሬ ግራ የሚያጋባ ስሜት ፈጠረብኝ:: ፋሲልን ተደግፌ ትንፋሼን ለመሰብሰብ እየሞከርሁ ..."ከየት መጥታችሁ ነው? ወዴት ናችሁ?" አለን አንድ ወጣት:: እንደ እኛው ሰው ይሁን የሞት መልአክ መለየት የምንችልበት ሁኔታ ውስጥ ስላልነበርን ሁለታችንም መልስ አልሰጠነውም:: ትቶን እስኪሄድ ድረስ ደግመን ልናየውም አልደፈርን::ብቻ በዚያች ሌሊት እንዲቃጠል ከተፈረደበት አንዱ የሆነው የእኛ ቤት በውስጡ ከነበረው ንብረት ጋር መታሰቢያው ጠፋ:: ሞትን በሩጫ ቀድመን ነፍሳችንን ማትረፍ ስለቻልን ራሳችንን ዕድለኞች አድርገን ቆጠርን:: በእርግጥም ዕድለኞች ነን:: መኖር ባይፈቀድልንስ?



ርዕስ ወደ ኂላ
ደራሲ ሊዲያ ተስፋዬ
ዋጋ 120ብር

◇◇

ፕሮፌሰር ጌታቸው ኃይሌ ሃገራችን ኢትዮጵያ ከኣሏት የግዕዝ ቋንቋ ሊቃውንት እና ምሁራን ዋንኛው የሆኑና ታላቅ የሃገር ባለውለታ ናቸው:: በግዕዝ ቋንቋችን ዙሪያም የበርካታ መጻሕፍት ደራሲ ናቸው:: በዚህ መጽሐፍ ግዕዝ ለመማር የሚፈልጉ ኢትዮጵያውያን የግዕዝ መጻሕፍትን ለማንበብ እንጂ በግዕዝ ቋንቋ ለመነጋገር ወይም ለመጻፍ ፍላጎት ኖሯቸው አይመስለኝም:: ይህ መጽሐፍ የተዘጋጀው ያንን መሰረታዊ ፍላጎታቸውን በግዕዝ መዝገበ ቃላት እርዳታ ለማርካት እንዲያስችላቸው ሆኖ ነው:: ግን እግረ መንገዳቸውን የቋንቋ ሂደት እንዴት እንደሆነ እንዲያዩ አልፎ አልፎ አንዳንድ ትችት ውስጥ እገባለሁ:: ግዕዝ ተማሪው ግዕዝንና አማርኛን ያንድ ቋንቋ ሁለት ቅርንጫፎች ያደረጋቸው ምን እንደሆነ ምክንያቱን ሰው ሳይነግረው በራሱ ተመራምሮ እንዲደርስበት መንገድ አሳየዋለሁ:: ፕሮፌሰር ጌታቸው ኃይሌ::



ርዕስ "ግዕዝ በቀላሉ" ከናሙና ድርሰቶች ጋራ
ደራሲ ፕሮፌሰር ጌታቸው ኃይሌ
የገፅ ብዛት 250 -
ዋጋ - 200 ብር

“ሃብታሙን በቀደሙት መፅሐፎቹ ማለትም በአውሮራ ፣ የሱፍ አበባ፣ እና ታላቁ ተቃርኖ እንዳገኘሁት የጠለቅ የኢትዮጵያ ታሪክ እውቀት አለው:: ስለ አንድ መሪ የግል ባሕሪያት ፣ ስለ አንዳንድ ታሪካዊ ምስጢሮች ለምሣሌ ስለ ታላቁ ኢትዮጵያዊ ኢኮኖሚስት መንገድ እንደዚሁም ለአንድ አውሮጵዊት አገር እንዲመሰልል የሰጠው መረጃ ለእኔ አስገራሚ ነበር:: ከዚህም በተጨማሪ ደራሲው አጉራ ዘለል እንዲሁም ጥራዝ ነጠቅነት በፍፁም አይታይበትም:: በተቻለው አቅም ሚዛናዊ ለመሆን ይጥራል:: ታሪክንም ላለማዛባት ትልቅ ጥንቃቄ ያደርጋል :: ይህ የመጀመሪያው ብቃቱ ነው::

ሁለተኛው እና አስገራሚው ብቃቱ ደግሞ የልቦለድ ድንቅ ፀሐፊነቱ ነው:: ገፀ ባህሪያቱ ፣ የታሪኩ ፍሰት ፣ የሴራው መጥበቅ ፣ የመቼት አቀራረፁ ፣ ልብ አንጠልጣይነቱ ፣ ጭብጡ (ከጭብጥም የኢትዮጵያ ታሪክ) ምን አለፋችሁ በአጠቃላይ ድንቅ ነው:: የገጣሚ ዮሐንስ ሞላ አስተያየት::

ርዕስ፡አስኳላ
ደራሲ፡ሀብታሙ አለባቸው
የገፅ ብዛት፡444
ዋጋ፡250 ብር



የሐሽማል መጽሐፍ ደራሲ የኔታ ሊቀ ሊቃውንት ሊቀ ጠበብት ማዕበል ፈጠነ አሁን ደግሞ በሌላኛው ስራቸው “ከርታታ ኮከቦች” መጥተዋል መልካም ንባብ ይሆንላችሁ ዘንድ ተመኘን::

ሐሽማል ከመሆናቸው በፊት የተዋነይን ውኃ መጠጣት ነበረባቸው:: ሁለቱ ተማሪዎች ከውኃዋ ከተጎነጩ በኋላ ሊቁ ፋሬስ አንድ ታሪክ መዘዙ:: “እኔና ቀለሙ ተፈሪ ይችን ውኃ የጠጣን ቀን ደስታው ሊያሳብደን ደርሶ ነበር:: ቀለሙ ከወሎ ሲመጣ ገና ብላቴና ነበር:: ኪነ ጥበብ ከሚባል ብስል ተማሪ ጋር መጥቶ የተዋነይን የቅኔ መንገድ ቀጻለ:: ከዚያ በፊት የዋድላውን የቅኔ መንገድ በደንብ ያውቀዋል:: የኢትዮጵያ ዐውደ ዓመት መባቻ ቅዳሜ ቀን በባተበት የዓመቱ መጨረሻ ቅዳሜ ቀን ከውኃዋ አብረን ጠጣን:: ክስተቷ በዚያ ቀን ነበር:: ከዚያ በፊት ያችን የምሥጢር ቀን ስንጠብቅ ዓመታትን አሳልፈናል:: ደጅ ጥናታችን የወግ አልነበረም:: ሕይወትን ፍለጋ እንደእኛ የተንከራተተ የለም:: ከርታታ ኮከቦች ነበርን:: ከመጽሐፉ የተወሰደ::

ርዕስ ከርታታ ኮከቦች
ደራሲ ማዕበል ፈጠነ
የገፅ ብዛት 443
ዋጋ 233 ብር



ስዓለም ከንፈ

ፎቶግራፈር በማርስ ላይ?

ማርስ ላይ ፎቶግራፈር?

ከመሬት በ2020 እ.ኤ.አ ተልካ በፌብሩዋሪ 2021 የማርስ ምድር ላይ ካረፈች በትጊዜ ጀምሮ የናሳዋ ፐርሰርቬራንስ ሮቨር (የአማርኛ አቻዊ ትርጉሟ አይገበሬ የሚለውን ቃል ሲይዝ) እስከ ዛሬ ድረስ ወደ ናሳ ጄት ፕሮፖልሽን ላቦራቶሪ (JPL) አስገራሚ እና አነጋጋሪ ምሥሎችን በተገጠሙላት ዘመናዊ ካሜራዎች አማካኝነት እየላከች ትገኛለች:: ዛሬ በሳይ-ቴክ አምዳችን ፐርሰርቬረንስ ምን እንደሆነች፣ ለምን ወደ ማርስ ዓለም እንደተላከች፣ እዛም ሄዳ ምን እንደምትሠራ እና ለሰው ልጆች የወደፊት የማርስ ተልዕኮ ምን ፋይዳ እንደምትጫወት እናያለን::

ፐርሰርቬራንስ ሮቨር ምንድን ናት?

ፐርሰርቬረንስ ናሳ ከዚህ ቀደም እንደላካቸው ሮቨሮች (ለምሳሌ ኪሪዮሲቲ) ሮቨሮች ማርስን ለማሰስ በ2020 ዓ.ም ከምድረ አሜሪካ የመጠቀች ሮቨር ናት:: ሮቨሮች በሰው ልጆች ተገጣጥመው በሌላ ዓለማት፣ ጨረዋዎች ላይ እዛው የዓለማቱ ምድር ላይ በመሄድ መረጃን የሚሰበስቡ ፣ በአርቴፊሻል ኢንተለጀንስ ታግዘው ስራቸውን በራሳቸው የሚሰሩ የሮቦት መኪናዎች ናቸው:: እንደው ለቃሉ አጠራር ነው እንጂ ውድ የህዋ መኪናዎች ናቸው ማለትም እንችላለን:: እነዚህ ሮቨሮች ከመሬር ላይ ካለ የቁጥጥር ጣቢያ ጋር በመገናኘት አልፎ አልፎ አስፈላጊ መረጃዎችን እና ትዕዛዞችን ይቀበላሉ ብሎም የሰበሰቡትን መረጃ መልሰው ይልካሉ:: ፐርሰርቬረንስም ተመሣሣይ ስራዎችን ማርስ ላይ ለመስራት ነው እንግዲህ በናሳው JPL ቁጥጥር አማካኝነት ቀድማ በ2020 መባቻ የተላከችው::

ለምን ማርስ?

እንደሚታወቀው፣ ከዚህ በፊት እንደተሰሩት ጥናቶችም ፤ ለመሬት ተቀራራቢ በሚባል መልኩ የሰው ልጆች አሁን ባለው የቴክኖሎጂ አቅማቸው ሄደው ለማጥናትም ሆነ ከተቻለ ለመኖር ካለንበት የፀሐይ ስርዓት ውስጥ ብቸናዋ አመቺ የሆነችው ዓለም ማርስ ብቻ ናት:: ይህም የሆነው ከስምንቱ ዓለማት ሁለቱ (ሜርኩሪ እና ቬነስ) ከፀሐይ ጋር ባላቸው ቅርበት ምክኒያት ከፍተኛ ሙቀትን በመያዛቸው፤ ዐራቱ የተቀሩት ዓለማት (ጁፒተር፣ ሳተርን፣ ኔፕቱን እና ዩራኑስ) ከጋዝ የተሰሩ በመሆናቸው ለመሬት ትንሽም እንኳን ቀረቤታ ያላት ዓለም ማርስ በመሆኗ ፤ መሬት ላይ ያሉ ታዋቂ የህዋ ሳይንሥ አጥኚዎች ማርስን ለማጥናት መርጠዋል:: ከቢሊዮን ዓመታት በፊት ማርስ ልክ እንደ መሬት ውቅያኖስ እና ህይወት ሳይኖርባት እንደማይቀር እና የውስጣዊ ሙቀቷ በመቀነሱ ምክኒያት ከባቢ አየሯን ማጣቷና ውቅያኖሶቿ ሚሽው እንደጠፉ የሚያሳዩ ጥናቶችን ተመልክተናል:: ይህንን ምክኒያት በማድረግ ናሳ ፐርሰርቬረንስን እዛው ማርስ ላይ ሄዳ መረጃዎችን እንድትሰበስብ ልኳታል::

ማርስ ላይ ከሄደች በኋላ ምን ትሠራለች?

ማርስ ላይ ከዚህ በፊት ህይወት ይኖርበታል የለባሉ ቦታዎች ቀድመው በተላኩት ሮቨሮች አማካኝነት ተለይተው ነበር:: ከእነዚህ ቦታዎች አንዱ ማርስ ላይ ያለው ጄዜሮ የተባለው ቦታ ነው:: ከታች በምስሉ ላይ እንደምትመለከቱት ይህ ቦታ በጥንት ጊዜ ወንዝ ይፈስበት የነበረበት እና ወደ ብዙ ገባሮች ተከፋፍሎ የሚጠፋበት ቦታ እንደሆነ መላ ምት ይቀመጣል:: ይህ የወንዝ መጨረሻ የነበረ ቦታ ለም አፈርን እና ለህይወት ምቹ የነበሩ ማዕድናትን ይይዛል ተብሎ ስለታመነበት አሁን ፐርሰርቬረንስ በዛ ቦታ ላይ ህይወት ስለመኖሩ ብሎም ኖሮ እንደሚያውቅ ለማጥናት ጥልቅ ጉድጓዶችን በመቆፈር ናሙናዎችን ትወስዳለች:: እነዚህን ናሙናዎች በቀጣይ ጊዜ በሚኖሩ ተልዕኮዎች አማካኝነት ወደ መሬት በማምጣት ጥልቅ የሆኑ ጥናቶች ይደረግባቸዋል:: በተጨማሪም ፤ ፐርሰርቬረንስ የሰው ልጆች በቀጣይ ወደ ማርስ ለመጓዝ እና ለመኖር እንዲያስችላቸው የሚያደርጉ የቴክኖሎጂ ሙከራዎችን ታካሂዳለች:: ከእነዚህም አንዱ ኦክስጅንን ከማርስ ከባቢ እንዴት ማምረት እንደሚቻል በተግባር በተገጠሙላት ቃኚዎች እና ላቦራቶሪ እማካኝነት መሞከር ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ተጨማሪ የውሃ ክምችትን ማሰስ ነው::



የፐርሰርቬረንስ ተልዕኮ ለወደፊት የህዋ ተልዕኮዎች ምን ጥቅም ይኖረዋል?

ፐርሰርቬረንስ አሁን የተላከችበትን ዓለማዎች ካሳካች ከዚህ በኋላ ሰዎችን ወደ ማርስ ለመላክ በሚደረገው ጥረት ላይ ትልቅ የቤት ስራን የምታቃልል ይሆናል:: የፐርሰርቬረንስ በማርስ ላይ ሙከራዎችን ሰርቶ ውጤቱን ወደ ምድር መላክ፣ የምስል እና ቪድዮ ማስረጃዎችን መሰብሰብ ብሎም ተጨማሪ ልዩ ልዩ ስራዎችን መስራት አሁን የሰው ልጅ ያለበትን የቴክኖሎጂ ልህቀት ከማመሳከሩም በላይ ለቀጣዩ ትውልድ መነሳሳትን የሚፈጥር ነው:: ከዚህ በታች ከናሳዋ ፐርሰርቬረንስ የተነሱ አስገሚ ምሥሎችን አያይዘናል:: ስለ ሮቨሯ ተጨማሪ ለማወቅ ወደ https://www.nasa.gov/perseverance ይሂዱ::

#ItsMyDam

ቅንነትን፣ ምክንያታዊነትንና ሀገር ፍቅርን በምትሰብከው አዝናኝ፣ አስተማሪና ወቅታዊ በሆነችው ቅንድል ዲጂታል መፅሔት ላይ ምርትና አገልግሎቶቻችሁን በማስተዋወቅ

ከ500 ሺ

በላይ ሰዎችን ይድረሱ!

0912178520
0920019699 ይደውሉልን!

ጸሐፊ ሁሴን ዩመር

በእጽማሜ ትንፏ ቆግኒት

ቢልጌትስ በሐብት የሚበልጠኝ አንድ ጥቁር ብቻ ነው አለ የአለማችን ቀዳሚ ባለጠጋ በአንድ ኢንተርቪው እንዲህ ተጠየቀ " ከአንተ የሚበልጥህ ባለጠጋ አለ ? " ‹‹ አዎ የሚበልጠኝ ሰው አለ። የሚበልጠኝ አንድ ሰው ብቻ ነው። ከብዙ ዓመት በፊት ወደ ኒውዮርክ መሄድ ነበረብኝ። ወደ ኒውዮርክ ለመሄድ አየር መንገድ ላይ ሳለሁ የተለያዩ ጋዜጦችን የጋዜጣ አዟሪዎች እጅ ላይ አየሁ፡ ፡ ካየኋቸው ጋዜጦች መካከል አንዱን ወደድኩት ለመግዛት አስቤ ኪሴ ስገባ ዝርዝር ስላጣሁ ሳልገዛው መልሼ ተውኩት። በድንገትም አንድ ጥቁር ጋዜጣ አዟሪ ልጅ መጣና ጋዜጣውን ሰጠኝ። ዝርዝር የለኝም አልወስደውም አልኩት እርሱም ችግር የለውም በነጻ ውሰደው አለኝና በነጻ ሰጠኝ። ከሦስት ወር በኋላ ተመልሼ በዚያው አየር መንገድ ማለፍ ነበረብኝና በዚያ አየር መንገድ ሳልፍ አሁንም አጋጣሚ ሆነና ያንን ጋዜጣ አዟሪ ጥቁር ልጅ አገኘሁት። አሁንም በነፃ ጋዜጣ ሰጠኝ። እኔም በነፃ አልቀበልህም አልኩት እርሱም ግድየለም ከትርፌ ላይ እቀንሳለሁ ውሰድ አለኝና በነጻ ሰጠኝ። ከ19 አመትም በኋላ ባለጠጋ ከሆንኩ በኋላ ያንን ልጅ ፈልጌ ለማግኘት ወሰንኩና ፈለኩት ከአንድ ወር ተኩል ፍለጋም በኋላ አገኘሁት፡ ፡ ከዚያም አወከኝ ብዬ ጠየኩት ። አዎ አውቅሃለሁ ዝነኛው ቢልጌት አይደለህም አለኝ። ከብዙ አመት በፊት ሁለት ጊዜ ጋዜጣ በነጻ ሰጥተኸኛል። ያንን ውለታህን አካክሼ መመለስ እፈልጋለሁና የፈለከውን የትኛውንም ነገር እሰጥሃለሁ ጠይቀኝ አልኩት። ያም ጥቁር ሰው በምንም መካካሻ ልትሰጠኝ አትችልም አለኝ እኔም " ለምን ? " አልኩት ። እኔ የሰጠሁህ ደሃ በነበርኩ ጊዜ ከድህነቴ ነው። አንተ ግን ልትሰጠኝ የመጣኸው ባለጠጋ በሆንክ ጊዜ ነው። እነዚህን ሁለቱን እንዴት አካክሰህ ልትሰጠኝ ትችላለህ፡ ፡" አለው። ቢልጌትም ያጥቁር ወጣት በርግጥም ከእኔ የሚበልጥ ባለጠጋ ነው።" እንዲል አደረገው።

ታዲያ ይህ የቢልጌትን የሀብት መጠን ወይም ባለጠጋነቱን እንዳያሥብ ያደረገው ሳይኖረው ከሌለው ላይ የሠጠው ጥቁር የገንዘብ እንጂ የመሥጠት ሃብታም እንዲየውም ቁጥር አንድ ቱጃር እሡ ነው ብሎ መሥክሮለታል ። ለመሥጠት ሃብታም መሆን አያሥፈልግም ፣ ከልብ ለጋሥ ለሆነ ሠው ።

"ለሁሉም ግዜውን ይጠብቅለታል
በማለት ሠለሞን ቀድሞ ተናግሮታል ! "

ብሎ ነበር ያዜመው ክቡር ዶ/ር አርቲስት መሐሙድ አህመድ። የኛነታችን ምሥጢር ከግዜ ጋር መሥተጋብር ፈጥሮ ትናንት ከትናንት ወዲያ አምና ፣ ካቻምና ፣ ዘንድሮ ቀን እና ለሊት በሚል የመሥፈሪያ አሊያም መዘወሪያ ግዜያችንን የምንጠብቅ ሥንቶቻችን እንሆን ? መልሱን ቤት ይቁጠረው ። እኛ የሠው ልጆች ወደዚህችኛይቱ ዓለም ስንመጣ ኖሩ ሞቱ ከሚባሉ ሠዎች ጎራ ላለመመደብ ምን ያህል እኛ ሥለራሳችን ሥለቤተሰቦቻችን ሥለጎረቤት ሥለ ሠፈራችን ሥለማህበረሠቡ እንዲሁም ምን ዓይነት በጎ ፋይዳ ያለው ሥራ ሠርተን እንድናልፍ አሥበን አሊያም ተመኝተን እናውቃለን ህይወት በራሷ መንገድ የምታሥተምርበት በርካታ እውነታዎችን ማሳያ የሚሆኑ ጥቂት ሠዎች አሉ ።

ለዛሬ ከላይ እንደመንደሬደሪያ ብዬ ያቀረብኩትን ፅሁፍ የሚያጠናክርልኝ ነውና አብራችሁኝ ሁኑ ። በዚህ ፅሁፌ እኔ አዲሥ አበባ ላይ ቁጭ ብዬ መጀመሪያ ወደጎንደር ከዛ ባህርዳር ይዣችሁ ልጓዝ ነው ።ሊቦ ከምከም አዲስ ዘመን ትውልድ ስፍራዋ ነው። ሠአዳ ንጋቴ ። ልጅ ሁና አርቆ አስተዋይ እና የልጅ ባህሪ ሳይሆን የአዋቂ አይነት ባህሪ ነበር የምታሳየው ።ማህበራዊ ኑሮ የልጅነት ልምምድ ውጤት ይመስላል ። በቤተሰብ ውሥጥ የሚወራባት እከሌ ሞተ ከተባለ ቀብር ላይ የምትታየው ከአዋቂ እኩል በመሆኑ ነው።ገና በአፍላ እድሜዋ የመሰረተቸው ትዳር አልሰመረም ነበር እና የስደትንም ህይወት ለማየት ህይወት አስገድዷት ነበር። በወቅቱ በኢትዮጵያውያንእህቶቻችንላይየሚደርሥባቸውእንግልትእናሥቃይእንቅልፍቢነሳትወደሃገሯተመለሰች።

ትንሹ እድሜዋ ግን ማየት ያለባትን ሁሉ ግን አሳያት:: አይኖቿ እስከአለማየት ደርሰው ነበር ፤ እግሮቿ የደረሰባቸው ጉዳቶች ትዳር ሥደት ብቸኝነት ሁሉንም ሆና አየችው ። የተቸገረ ፤ የተራበ ፤ የተጠማ ፤ የታረዘ ፤ አይታ ማለፍ አትችልም:: እጆቿ መሥጠት እሥከቻሉ ድረሥ ትዘረጋለች ። እቤታቸው ውስጥ ትርፍ ነገር አይታሰብም ።ልባሽ ልብሶችን ማናችንም ለሰው ልንሰጥ እንችላለን ።ነገር ግን የአልጋ ልብሥ ከቤት ደብቆ የበረደን ሠው ማልበሥ የማይታመን ደግነት ይመሥላል ልጅት ግን አድርገዋለች::

ጌታለም የተዘነጋ ፤ አሥታዋሽ ያጣ ፤ ህይወቱን በጎዳና የሚመራ ከህይወት መሥመር ከወጣ ቆየት የሚሉ ክፉ የመከራን ወቅቶች በራሱ ዓለም ሲመራ የቆየ በአእምሮ ህመም የሚሰቃይ ሠው ነው ።እሡንም ሠዎች አይረዱትም ጌታአለምም ማንንም አይረዳም አይቀርብም ። ግና ሳይደግሥ አይጣላምና ጌታ ዓለምን ከወግዲ ሠአዳ ንጋቴን ከሊሞ ከምከም ባህርዳር አምጥቶ አገናኛቸው ። ሠአዳ መክሊቷን ፍለጋ ላይ ናት ግን እንዴት እና መቼ የት እንደሚሆን ግን ፈፅሞ አታውቀውም ።

ይህች በደግነት ሚዛን ላይ እኩል ተደርጋ የተሠራች ወጣቷ ሠአዳ ንጋቴ ከአረብ ሃገር ሥደት ሥትመለሥ በቀጥታ የሔደችው እንጅባራ የሚኖረው ወንድሟ ጋር ነበር ።የእንጅባራ ከተማ አሥተዳደር ከሥደት ተመላሾችን እራሳቸውን እንዲችሉ በተደረገ ጥረት ውሥጥ ከሥደት ተመላሽ ሥለመሆኗ ያላትን ማሥረጃዎች በመያዝ የእንጅባራ ከተማ አሥተዳደር በአነሥተኛና ጥቃቅን ውሥጥ ቁርሥ ቤት ከፍታ የራሷን ህይወት መምራት ጀመረች ።

ወጣቷ ሠአዳ እንጅባራ ከተማ ዋግ ህምራ አደባባይ ሽሮ ቤት ከፍታ እየሰራች ነው ።ግና የምታየውና የምትሰማው የህሊና እረፍት ነሳት እንጅባራ ከተማ ዋግ ኽምራ አደባባይ ተብሎ በተሰየመው የከተማዋ ማዕከላዊ ክፍል የለየለት በሚባል ደረጃ ልብሱን የጣለ፣ የሚመገበውን ከአፈርና ጠጠር ለይቶ የማያውቅ በተቀመጠበት የሚጸዳዳና በላዩ ላይ ያለው ጸጉር በከፍተኛ ሁኔታ ያደገና ተባይ በግልጽ የሚታይበት ጎልማሳ ሁልጊዜም በጸጥታ ይታያል:: ጎልማሳው ከየት እንደ መጣ ወደ አካባቢው መቸ እንደመጣ የሚያውቅ ሰው የለም:: በዚች አደባባይ ላይ ግን ለሰባት ዓመታት አንዳች ነገር ሳይናገር ተቀምጦ መታየቱ የዘወትር ትዕይንት ነው:: ምንም ይሁን ምንም አንዳች ቃል ሲናገር ተሰምቶ አይታወቅም:: ረሃብ ሲጸናበት ቀንም ሆነ ሌሊት በመጮህ እጆቹን ሲነክስ ከታዬ የአዕምሮ ሕመምተኛው ጌታለም መርቻው ርቦታል ማለት ነው::

ባልጠበቀችውና ባልገመተችው ሠዓት የሠአዳ መክሊት በጌታለም ውድቀት ውስጥ ካልተገለጥኩ እያለ ይታገላት ጀመር ። ነገሩ የታይታ ፍላጎት አልነበረምና ከውሥጥ ፈንቅሎ የሚወጣ ማንነቷ ለማመን የሚከብድ እንዲሁም በሴት ልጅ አቅም ይቻላል የማይባል ትልቅ ገድል ሀ ብላ ጀመረች በድልም ተወጣችው::

ከዛም ማንም ይሆናል ብሎ ከማይገምተው ጎዳና አንስታ ከራሷ ጋር በዛች ጠባብ ኮንቴነር ውሥጥ በማኖር በፍቅር የተዋበ ደግነቷን አሳየችን ። በእድሜ ገና ብዙ ያልተራመደችው እንሥት ሠአዳ ንጋቴ ። ዛሬ ጌታአለም አዲሥ ሠው አዲሥ ማንነትን ተላብሧል ይህንን የበጎነት ሥራዋን የተመለከቱ ሁሉ አድናቆት ይቸሩዋት ጀመሩ በየማህበራዊ ሚዲያዎች ላይ መነጋገሪያ ሆነች ።

ሠአዳ ንጋቴ አንዴ የተፈጠረችበት አላማ ለዚህ ነበርና ጌታለምን ከወላጆቹ ጋር ካገናኘችው በኋላ ለዓመታቶች ልብሥ ያልቀየረውን ወጣት ከወደቀበት በማንሳት በሚያሥገርም ፍጥነት የተሻለ ሠው ሆኖ ወደማህበረሠቡ እንዲቀላቀል አስቸጋሪ ግዜዎችን እየታገለች ትገኛለች ። ወጣቷ የበጎ ሰው እንቅልፍ የላትም የተቸገረ የወደቀ አለ በተባለበት ሁሉ ቀድማ ትደርሳለች:: ቤቷን ዘግታ ካገር ሃገር ለሠው ልጆች ፍቅር ለመሥጠት የዘወትር ሥራዋ ነው ። ዘር ቀለም ሐይማኖት አይገድባትም ። ድንበር የለሽ የሰላም ለጋስ የፍቅር የመሥጠት ተጓዥ ናት ።

ሴት ናት በዛ ላይ ወጣት ብዙ ነገሮችን ተቋቁማ እንደወፊቷ ከእጇ ቢያጥራት የአፏን የምታካፍል ለብዙዎቻችን ምሳሌ የምትሆን ወጣት ናት::

ከላይ መግቢያዬ ላይ የተጠቀምኩት የቢልጌት ታሪክ ። ለዚህች ታዳጊ የበጎነት ፈርጥ ግዜ ሠፍሮ ቀን ቆጥሮ የሚመሠክርላት መምጣቱ አይቀሬ ቢሆንም ። እይታን እና እውቅናን ፈልጋ ሣይሆን የተፈጠረችበት ፅኑ አላማ ነውና ወጣት ሰአዳ ንጋቴ ነገ ትልቅ ደረጃ ላይ ደርሳ እንደምናያት እግርጠኛ ነኝ ። “ የሚያጠግብ እንጀራ ከምጣዱ ያሥታውቃልና ! “ አበቃሁ::



ጌቱ በቀለ በዳዳ

መምህራን

እንኳን ለአዲሱ ዘመን አደረሳችሁ ውድ የቅንድል ድጅታል መጽሄት አንባቢያን:: ሰላማችሁ ይብዛ:: ለዛሬ ላስነብባችሁ የፈለኩት ስለ መምህራን ነው:: ስለ ጥንታዊ የኢትዮጵያ መምህራን:: ኢትዮጵያን ትውልድ እንዲጠብቃት ታላቁን ዎጋ የከፈሉትን ጥንታውያን የኢትዮጵያ መምህራን ክብር የሚገባቸው ቋሚ ታሪክ ያላቸው የኢትዮጵያና ትውልዷ ባለውለታ ናቸው:: በህይወት ላሉት ሽልማት ላለፉት ደግሞ መታሰቢያ ሐውልት ሊቆምላቸው ፤ የመታሰቢያ ቀን ከአመቱ ቀናት ውስጥ ተመርጦ ሊከበርላቸው ይገባል::

ትናንታችንን ዞር ብለን ካስተዋልን እነዚህ ሊቃውንት ሁሉ ለሀገራችን ታላላቅ ስራን የሰሩ እውቀትን በነጻ ያካፈሉ፤ በኢትዮጵያ ታላቅ ዝናን ያተረፉ ናቸው:: ይኽን ሁሉ ሞያና የሀገር ባህል የጠበቁና ያስተላለፉ፤ ሕዝባችንን ስልጣኔን ይዞ እንዲቆይ በቀላሉም ለመጪው ትውልድ ለማስተላለፍ የቻሉ እነርሱ ባስተማሩት ትምህርት ነው::

ህዝቡን ህዝብ አድርገው ሐሞተ ቆራጥና ደፋር አድርገው ለነጻነትና ለሃይማኖቱ ተጋዳይ እንዲሆን የሰሩና ያስተማሩ እነርሱ ናቸው::

ሀገሩን አፍቃሪ መንግስታቸውን አክባሪ በጠቅላላው የያዘውን ሁሉ ጥቅሙንና ጉዳቱን አውቆ ኢንዲኖርና መመሪያ የሰጡ እነርሱ ነበሩ:: ይሄን ሁሉ ለማድረግ የቻሉት ግን የኢትዮጵያ መምህራን መከራ የማያሸንፋቸው ፤ ማግኘትና ማጣት ቢፈራረቅባቸውም ግምት የማይሰጡት፤ በረሃብ የማይፈቱ፤ ማዕረጋቸውን እንጅ ሆዳቸውን የማይወዱ አባቶች ስለነበሩ ነው:: አባቶቻችን ትልቅ እውቀት የነበራቸው ናቸው :: ስለዚህ በባህረ ሀሳብ በቀላሉ የሚዋኙ ለጥበብ በቃኝ የማይሉ ነበሩ:: ሞያችን እና ስልጣኔያችን እንዳይጠፋ በማለት ተርበው ከመማራቸው ይልቅ ተርበው ማስተማራቸው በሰፊው ይነገርላቸዋል::, በማግኘታቸውም ሆነ በማጣታቸው ቸል ሳይሉ እውቀት ሲዘሩ ሀገራቸውን ከአፍሪካ ለይተው የእውቀት ምንጭ የነጻነት መዝገብ አድርገው መቆየታቸው የታወቀ ነው::

ዛሬን ከሃሳብ ፌርማታ አረፍ ብሎ ስለ ጥንታዊ የኢትዮጵያ መምህራን የሊቃውንትነታቸውን የእውቀት ጥልቀት፤ በእነርሱ ዘመን ስለሰሩት ባህላችን ዞር ብሎ የሚመረምር ባለመኖሩ ታላቁን ውለታቸውን ግምት ሊሰጥ የቻለ የለም:: ጥንታዊ እውቀታቸውም ከቀን ወደ ቀን እየኮሰሰና እየተዋረደ ይገኛል:: በጥንት ዘመን የሆነ እንደሆነ መምህራን በአንድ አይነት እውቀት ሳይወሰኑ የጠፋውን በመፈለግ የደከመውን በማጽናት ከእውቀት ወደ እውቀት ይራመዱ ነበር:: አንድ መምህር ከሁለትና ሶስት አይነት እውቀት በላይ ስለአለው ያን እውቀቱን በህይወት ሳለ ለማካፈል ሲል ልእይወቱ ሳይሳሳ ለተማሪው በሚመቸው ሀገር እየዞረ እየተንከራተተ ያስተምር ነበር:: ለማስተማርም አሁን በኋላ ነገ በማለት ጊዜ ሳይወስን በቀን በሌት ያለ ግዜ ገደብ ያስተምር ነበር:: ለዚህ ሁሉ ድካሙ ተመጣጣኝ ክፍያን የሚከፍለው አልነበረውም:: ህዝቡኳ ቢቀጥረው እርሻ ቢያርስለት ከአዝመራው ጥቂት ለእለት ጉርሱ ቢሰጠው እንጅ ለኑሮውና ትዳር ላላቸውም በቂ ወረትን አይቋጠርለትም ነበር::

መምህሩ ሁሉንም የችግር ግትልትሎሽ ሳያስበው በማስተማሩ ብቻ እየተደሰተ መንፈሱ ጸንቶ ችግሩን አሸንፎ ይኖራል:: ቤት ውስጥም የሚገጥመውን የወቀሳ ፈተና ከቁብም ሳይቆጥር ትውልድን በመተካቱ ትጋቱ ይበረታበታል:: አንዳንዴ ያለእረፍት ሌተ ቀን በማስተማር በማሳለፉ ለትዳሩ የሚሆን ወረትን ባለማምጣቱ እራት በሚጠይቅበት ግዜ ሚስቱ ተናዳበት ከመሶቡ ድኅን ከድና አቅርባለታለችም ይባላል::

ጥንታዊ መምህራን የሚገጥማቸው ፈተና ተነግሮ አያልቅም:: ሲያስተምሩ በመቆየታቸው የሚጎዱ በበሽታ ተሰነካክለው የእድሜ ልክ በሽታን የሚያተርፉ ሲሰቃዩ የሚኖሩና ብዙ ማገልገል እየቻሉ ባጭሩ በሞት የሚለዩን ስፍር ቁጥር የላቸውም ነበር:: ይሄን ሁሉበየዘመኑ ዎጋ እየከፈሉ ሀገርን ለማስቀጥል ሀገር በቀል እውቀትን ለማስፋፋት የዋሉትን ውለታ ከቁም ነገር ያልቆጠረው የመጣው ስርዓት በኮረጃቸው የትምህርት ፖሊሲዎቹ ውስጥ ለነሱ የማስተማር ጥግን ባለመተው በሃገርና ትውልድ ላይ የበዙ ውጥንቅጦች እንዲፈጠሩ ክፍተቶች ተፈጥሮአል::

ኢትዮጵያ በትምህርት የረዥም ግዜ ታሪክ እንዳላትና በ4ኛው መቶ ክዘመንመንፈሳዊ ስለመጀመሩ ታሪክ ይናገራል:: በሁለቱ ትላልቅ ሃይማኖቶች ውስጥ ባሉ ጥንታዊ መምህራን ለህዝቡ ጠቃሚ የሆኑ ባህላዊ አልባሳትና ቁሳቁስ ስርዓት ስነ ቃላዊ እሴቶችን አውርሰውናል

መምህራን የቀጠለ . . .

ኢትዮጵያ ከክርስቶስ ልደት 100 ዓዓ በፊት ጀምሮ በምትጠቀምበት የግዕዝ ፊደላት ሙህራንዋ ለትውልዱ ፍልስፍናን ሃይማኖትንና ስርዓተ ንግስናን በማስተማር ከትውልድ ትውልድ በማስተላለፍ ከአፍሪካ ልዩ ሀገረ ኢትዮጵያን አዋልደውልናል።

በተለይ ከክርስቶስ ልደት በኋላ በንጉስ ኢዛና ዘመን የቤተ ክህነት ትምህርትን እንደተቀበለችና ሃማኖትም እንደተስፋፋ፣ መጽሃፍ ቅዱስም በ4ኛው መቶ ክዘመን ወደ ግዕዝ እንደተተረጎመ ሃይማኖታዊ ትምህርትም በ5ኛው መቶ ክዘመን እንደተጀመረ የታሪክ ድርሳናት ያወሳሉ።

በወቅቱ በብሄራዊ ቋንቋነት ኢትዮጵያ ስትገለገልበት በነበረው ግዕዝ ቋንቋ የተጻፉት መጽሃፈ ፈላስፋና ክብረ ነገስት ባህላዊ ትምህርትን ለመስጠት ከፍተኛ ድርሻ ነበራቸው። ጽህፈት ቅኔ ዜማ ገድል ታምራት ወዘተን በግዕዝ ተጽፈው ለትውልድ እንዲተላለፉ መምህራን ከፍተኛ ሚናን ተወጥተዋል።

እነዚህን እውቀቶች ለመማርም እስከ 30 ዓመታት ጊዜን ይፈልጉ፣ መምህሩም እጅግ የበዙ መስዋህትነትን ይከፍሉ እንደነበር የታሪክ ተመራማሪዎች ይናገራሉ። በቤተ ክህነት የተማሩ ሊቃውንታትም በዳኝነት በአስተዳደር በጸሃፊነትና በሌሎችም የሲቭል ስራዎች ላይ ግልጋሎት ይሰጡ ነበር።

ሙሁራን ኢትዮጵያን እዚህ እንድትደርስ በየዘመናቱ ለከፈሉት ተመን የለሽ ዋጋ ይሁንታን የነፈጉ ስረአተ መንግስታት በሚያወጧቸው የትምህርት ፖሊሰዎቻቸው ክቡሩን ሙያ አቅለውታል። ከእውነተኛ ሙሁር ይልቅ አድርባይን ቀፍቅፈዋል። በእጅ አዙር በስማቸው እና በስራቸው በገቡ ቁጭ በሉ ሙሁር በሚያበራዩት ክፉ እውቀት የትውልድን ተስፋ አጨልመዋል።

ያም ሆነ ይህ በሀገር ቋሚ ህያውና ተዳሳሽ ታሪካዊ ቅርሶችዋ ጀርባ ደማቁን የእውቀት አሻራ ያሰፈሩ ከትውልድ ወደ ትውልድ እንዲተላለፍ ወደር የለሽ እና ተመን አጥ ውለታን ለዋሉት ሙሁራኗ ፤ኢትዮጵያ መዘከር እና መታሰቢያ ቀንን ልትበይንላቸው ይጠበቃል።አሁንም የጥንታዊ መምህራንን ፈለግ ይዘው በእውነተኝነትና በቅንነት ሀገራቸውንና ትውልዳቸውን እያገለገሉ ላሉትም ሀቀኛ መምህራን ተገቢ ክብርና ወረት ልትጀብናቸው የገባል።

ማንበብ አለማወቅን ይገልጻል።
ከማማረር ማምረር።
በድንቁርና ላይ እናምጽ።

ለምንጭነት
የኢትዮጵያ ትምህርት ችግሮች ያስከተሉት ኪሳራና መፍትሄዎቹ- በተስፋዬ ለጋ 2005ዓም
እና
ጥንታዊ የኢትዮጵያ ትምህርት- ሊቀ ስልጣናት ሀብተ ማርያም ወርቅነህ 2013 ዓም እትምን
ተጠቅሜያለሁ።

ማውጫ
የቅንደል መለከት ለኢትዮጵያውያን...!
KendelM

ቅንደል
DIGITAL MAGAZINE
"...ለመታረቅም ሆነ ለመጣላት ሀገር ስለሚያስፈልገን በቅድሚያ መሸማገያችን የሆነችውን ኢትዮጵያን ለማቆየት እንስራ....."
አርቲስት መቅደስ ፀጋዬ
ሀገሬ
የቅንደል መለከት ለኢትዮጵያውያን...!
ሳይ-ቴክ
ደመናን ማበልጸግ (Cloud Seeding)
መስከረም 1 2014
ESQUARE ADVERTISING
" . . . . አብረን ስንጓዝ ተገጫጭተን፣ ተገፋፍተን ሊሆን ይችላል፡፡ሆኖ ተስፋችን ስንል ግን ስብራታችንን የፍቅር ንቅሳት አድርገነው ወደፊት ልንጓዝ ይገባል. . . "
ድምፃዊ ሀይለየሱስ ፈይሳ
ሀገሬ
ሀገር አንቁ ጣጣሽ - ያሳር ክንድሽ አቅፎን !
አጃኢብ
ምኞት ያሰከረው የሰው ልጅች የዘመን መሰወጫ
ሳይ-ቴክ
ፎቶግራፈር በማርስ ላይ?
"ቅንነት ደል ያደርጋል"
ንጉሳ አወት
የሕይወቴ ቅኝት